ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
MINISTRY OF INDUSTRY

# የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
## የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂ

2016 – 2022

ሚያዚያ 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
MINISTRY OF INDUSTRY

# የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
## የኮርፖሬት ኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ

ሚያዚያ 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ገፅ


ምዕራፍ አንድ 1

መግቢያ 1

1. ተቋማዊ ኮሚኒኬሽን /organizational communicastion ---- 1
2. የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ አስፈላጊነት ---- 1
3. ስራቴጂው የተዘጋጀበት መንገድ ---- 2
4. የስትራቴጂው ተፈጻሚነት ወሰን---- 4
5 የኮምዩኒኬሽንስትራቴጂው አፈጻጸም ሁለትምዕራፎች---- 3
3 የኢንዱስትሪ ዘርፍ ኮምዩኒኬሽን ዳሰሳ---- 3
4. የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂው መነሻዎች---- 4
4.1. የኢትዮጵያ ታምርት የንቅናቄ እቅድ እንደ መነሻ ---- 4
4.2. የአምራች ኢንዱስትሪ ረቂቅ ፖሊሲ---- 4
4.3. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ እንደመነሻ ---- 5
4.4. የዓለም አቀፍ እና ሀገር ውስጥ የተቋማት የአምራች ዘርፉ የኮሙኒኬሽን ስራዎች ተሞክሮ ---- 5
4.5. የዓለም አቀፍ ተሞክሮ ---- 5
4.6. የሀገር ውስጥ የፌዴራል ተቋማት የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ዝግጅት ተሞክሮ ---- 5
4.7. የአምራች ኢንዱስትሪ ምንነት እና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ---- 7
5. የስትራቴጂው የተፈጻሚነት ወሰን ---- 7
6. የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂው ግብ ---- 8
7. የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂው ዓላማ ---- 8

ምዕራፍ ሁለት ---- 9

2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኮሚኒኬሽን የነባራዊ ሁኔታ ትንተና ---- 10
ሰንጠረዥ 1. የጥንካሬ እና ደካማ ጎኖች የSWOT ትንተና 2015 ---- 10
ሰንጠረዥ 2. መልካም አጋጣሚና ስጋት የSWOT ትንተና 2015 ---- 11

ምዕራፍ ሶስት ---- 12

3.የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኮሚኒኬሽን ራዕይ፣ተልዕኮ እና ዕሴቶች ---- 13
3.1 የስትራቴጂው መርሆዎች ---- 13
5. የመረጃዎች ባህሪያት ---- 14
5.3. ሰንጠረዥ3 የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባለድርሻ አካላት ትንተና ---- 14
7. የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ግቦች ---- 17
8. በምዕራፎች የተከፈለ የስትራቴጂያዊ ግቦች የድርጊት አፈጻጸም እቅድ---- 21
9. ቁልፍ ስትራቴጂካዊ የኮምዩኒኬሽን መልዕክቶች ---- 26
10. በተቋሙ ውስጥ ያሉ የኮሚኒኬሽን ተግባራት /ስራዎች ---- 29

ምዕራፍ አራት ---- 30

4. ኮሚኒኬሽን ፕሮቶኮል ---- 31
4.1. ከኮሚኒኬሽን አንፃር ያሉ የህግ ጉዳዮች ---- 31
4.1.1. መረጃ የማግኘት መብት ---- 31

ምዕራፍ አምስት ---- 32

5. ክትትልና ግምገማ ---- 33
5.1. የዕቅድ ዝግጅት ሥርዓት ---- 33
5.2. የድጋፍና ክትትል ስርዓት ---- 33
5.3. የግምገማ ስርዓት ---- 34
5.4ማስፈጸሚያ ስልት ---- 34
ማጠቃለያ ---- 36

- የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ በጀት ---- 37

**የሚኒስትሩ መልዕክት**



# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.ተቋማዊ ኮምዩኒኬሽን /organizational communicastion

የኮምዩኒኬሽን ሥራ የአንድን ተቋም እቅድ፣ ተግባርና የወደፊት አቅጣጫ ለህዝብና ለባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅን፣ ዘላቂ የገጽታ ግንባታ ማካሄድን፣ ከተገልጋዮች ጋር የግንኙነት ድልድይ መፍጠርንና የተቋሙን ፍላጎት ከባለድርሻ አካላትና ከህዝብ ፍላጎቶች ጋር በማጣጣም ማስኬድን አካቶ የያዘ ቁልፍ የአመራር ተግባር ነው።

ኮምዩኒኬሽን መልዕክት ላኪና ተቀባዮች ሲኖሩት በተቋም ውስጥ የሚካሄዱ የውስጥ ግንኙነቶችንና ከባለድርሻ አካላት እንዲሁም በአምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል የሚከናወን የውጪ ግንኙነትን ያካተተ ሂደት ነው። በሠራተኞች መካከል የሚፈጠር የእርስ በእርስና ሙያዊ ግንኙነት የተለያዩ የኮምዩኒኬሽን አማራጮች ማለትም የገፅ ለገፅ፣ ኢሜይል፣ ማህበራዊ ሚዲያና የመሳሰሉት ያሉ ሲሆን፤ ማስታወቂያዎች፣ ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ የተቋም መለያ ብራንዶች...ወዘተ ለውጫዊ ኮምዩኒኬሽን አገልግሎት ከሚውሉ የመገናኛ ዘዴዎች (የኮሚኒኬሽን መንገዶች) መካከል ይጠቀሳሉ። ስለሆነም የትኛውም ተቋም እቅዱን፣ ተግባሩንና የወደፊት አቅጣጫውን ስኬታማና ውጤታማ ለማድረግ የተቋሙን ኮምዩኒኬሽን ይበልጥ ማጠናከርና ስትራጂያዊ በሆነ መንድ እንዲመራ ማድረግ ይገባዋል።

ይህ የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ በሁለት ምዕራፎች ተከፍሎ የሚተገበር ሲሆን፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ ያሉት አራት ዓመታት ማለትም ከ2016 እስከ 2019 (የኢትዮጵያ በጀት ዓመት) የግንዛቤ ፈጠራና የአመለካከት ለውጥ ሥራዎች በስፋት የሚተገበሩበት ሲሆን፣ በሁለተኛው ምዕራፍ ያሉት ሦስት ዓመታት ማለትም ከ2020 እስከ 2022 በመጀመሪያው ምዕራፍ ሲሠሩ የነበሩ ሥራዎችን በማጠናከር የትግበራ፣ የባለቤትነት ስሜት የመፍጠርና የባህል ሽግግር ማምጣት ላይ መሠረት ያደረጉ ሥራዎች የሚተገበሩበት የስትራቴጂው የድርጊት ምዕራፍ አቅጣጫዎች ናቸው።

## 2. የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ አስፈላጊነት

ስትራቴጂያዊ ኮምዩኒኬሽን አንድ ተቋም ለህልውናውና ለዘለቄታዊ ስኬቶቹ ሲል ከተለያዩ አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን የታቀዱ የመረጃ ልውውጥና የግንኙነት ጥረቶችን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ፅንሰ ሀሳብ ነው። ተቋማዊ ኮሚዩኒኬሽን የሚካሄደው ውስብስብና ተለዋዋጭ በሆነ አውድ ውስጥ ሲሆን እንደ ባህል፣ የሐሳብና የግብ ልዩነቶች፣ የስልጣን ተዋረድ፣ መዋቅሮችና የመሳሰሉት ኮምዩኒኬሽን ግቡን መምታት እንዳይችል ሊያደርጉ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም የኮምዩኒኬሽን ተግባራትን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለመምራትና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን ግቦች ለማሳካት ስትራቴጂያዊ እይታ ያለው የኮምዩኒኬሽን አካሄድ መተግበር አስፈላጊ ነው።

በዚህ የስትራቴጂ ሰነድ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው አንደኛው ጉዳይ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና የተጠሪ ተቋማት አመራርና ሠራተኞች ስለተቋማቸው ተልዕኮና በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለማምጣት ስለታሰቡት ዕድገቶች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በሐላፊዎችና በሠራተኛው እንዲሁም በሥራ ክፍሎችና በሠራተኞች መካከል ግልፅ፣ ፈጣንና ተማምኖ ለአንድ ዓላማ በትብብር የመሥራትን ባህል ለመፍጠር የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂው የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡
በሌላ ወገን ከሕብረተሰቡ፣ ከዘርፉ ባለድርሻ አካላትና ከአጋሮች ጋር የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ፣ የግንዛቤ ፈጠራና የአመለካከት ለውጥ እንዲሁም የማሳመንና የአምራች ኢንዱስትሪውን ሚና አጉልተው የሚያሳዩ ተፅዕኖ ፈጣሪ ተረኮችን የመፍጠሩ ሂደት በስትራቴጂ መመራቱ ለውጤታማነቱ የተሻለ ዋስትናን ይሰጣል፡፡ የክትትልና ግምገማ ሥራም የስትራቴጂው አካል በመሆኑ የጥረቶቹ ውጤታማነት በየወቅቱ እየተመዘነ ትምህርት የሚወሰድበትና እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያም የሚደረግበት ይሆናል፡፡
ኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ለምን፣ ለማን ምን ዓይነት መልዕክት መተላለፍ እንዳለበት ቀድሞ ይለያል፡፡ ጥሩ የሆነ የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ አንድ ተቋም ከባለድርሻ አካላት፣ ከመገናኛ ብዙሀን፣ ከደንበኞች እንዲሁም ከሠራተኞች ጋር ምን ዓይነት ኮምዩኒኬሽን በምን ዓይነት መንገድ መደረግ እንዳለበት አቅጣጫ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ውጤታማ የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ መኖርና መተግበር በሥራ ቦታ ያለውን አጠቃላይ ምርታማነትን ለማሳደግ ያስችላል፡፡ ተቋሙ በኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግሩ ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ ከሠራተኞች፣ ከባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከአገልግሎት ፈላጊዎች/አምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር የመተማመን ስሜትን እንዲፈጠር ያግዛል፡፡

## ስራቴጂው የተዘጋጀበት መንገድ

በተቋሙ የበላይ አመራር አነሳሽነትና አቅጣጫ ሰጪነት ይህ የኢንደስትሪ ዘርፍ የሰባት ዓመታት የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡ የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂውን ለማዘጋጀት ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት እንዲሁም ከሚዲያ አካላት የተውጣጣ ኮሚቴ እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ በዚህም ቀድሞ በዘርፉ የተከናወኑ ሥራዎችን፣ የዘርፉን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ እና የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ሠነዶችን በመዳሰስ በግብዓትነት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተመረጡ የዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ተቋማት የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂዎችን በመፈተሸ፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ የዘርፉን የጥናትና ምርምር ሠነዶችንና መጻሕፍትን በመዳሠስ ጠቃሚ መረጃዎችን ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ ከዘርፉ ከፍተኛ አመራሮች፣ ከተጠሪ ተቋማት ሃላፊዎች፣ ከዘርፉ የክልል የሕዝብ ግንኙነት አመራሮችና ከሚዲያ ባለሙያዎች ጋር ውይይት በማድረግ በዘርፉ ያሉ ክፍተቶችንና ጠንካራ ጎኖችን ለመለየትም ጥረት ተደርጓል፡፡ እነዚህን መነሻዎች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀውን ረቂቅ የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአመራር አባላት ቀርቦ ገንቢ አስተያየቶች ከተሰጡበት በኋላ የማሻሻያ ሥራዎች ተሠርተውበት በዚህ መልክ ቀርቧል፡፡

## የስትራቴጂው ተፈጻሚነት ወሰን

ስትራቴጂው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በ10 ዓመት የመሪ ዕቅዱ የያዛቸውን ተልዕኮዎች ለማሳካት እንዲያስችል ለሚከናወኑ የኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች ለቀሪ ሰባት የመሪ ዕቅዱ ዓመታት ማለትም ከ2016 እስከ 2022 በጀት ዓመት የሚመራበት ነው፡፡ ይህ ስትራቴጂ በዋነኝነት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ እንዲሁም በተጠሪ ተቋማትና በክልልና በከተማ አስተዳደር የኢንደስትሪ ቢሮዎች የኮሚዩኒኬሽን አደረጃጀቶች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂው አፈጻጸም ሁለት ምዕራፎች

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መሪ ዕቅድ ተግባራዊ በሚሆንባቸው 10 ዓመታት፤ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት የሙከራ፣ ቀጥሎ ያሉት አምስት ዓመታት የትግበራ፣ ቀሪዎቹ ሁለት ዓመታት የባለቤትነት ተግባራት እንዲሆኑ አቅጣጫ ተቀይሷል፡፡ የኢንደስትሪ ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂክ እቅድም ይህን ታሳቢ ያደርጋል፡፡
ስለሆነም የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ለእቅዱ ስኬት የሚጠበቅበትን ተግባር እንዲያከናውን ሥራ ላይ በሚውልባቸው ሰባት ዓመታት የሚከናወኑ ተግባራትን በሁለት ምዕራፎች መክፈል አስፈልጓል፡፡ በተጨማሪም ተግባራቱ ይህን ስትራቴጂ ለማስፈጸም በሚዘጋጀው የድርጊት መርሃግብር ላይ ተለይተው ተገልጸዋል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

ምዕራፍ አንድ፡-
ከ2016 — 2019 በጀት ዓመት ባሉት አራት ዓመታት የውስጥና የውጭ ኮሚዩኒኬሽንን በማጠናከር በተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞች፣ በተጠሪ ተቋማት፣ በክልልና በከተማ አስተዳደሮች የኢንዱስትሪ ቢሮዎች፣ በአምራች ኢንዱስትሪዎችና በሌሎችም ባለድርሻ አካላት የጋራ ተሳትፎ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ሰፊ የግንዛቤ መፍጠሪያና የአመለካከት ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የኮምዩኒኬሽን ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

ምዕራፍ ሁለት፡-
ከ2020 — 2022 በጀት ዓመት ያሉት ቀሪዎቹ ሦስት ዓመታት በምዕራፍ አንድ በተከናወኑት ተግባራት ላይ በመመርኮዝና ከላይ የተጠቀሱትን ባለድርሻ አካላት ይበልጥ በማሳተፍ፤ የግንዛቤ ማጎልበቻ ተግባራትን የማከናወን፣ የባህል ሽግግር የማምጣት፣ የባለቤትነት ስሜት የመፍጠርና የሚመለከታቸውን አካላት ትርጉም ያለው ተሳትፎ የማረጋገጥ ሥራዎች ላይ ያተኩራሉ፡፡

## 3. የኢንዱስትሪ ዘርፍ ኮምዩኒኬሽን ዳሰሳ

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና በተጠሪ ተቋማት የኮምዩዩኒኬሽን መዋቅር አማካኝነት ለሠራተኞች፣ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች፤ ለባለድርሻ አካላት የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃ ተደራሽ እየተደረገ ይገኛል፡፡
ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በየደረጃው ያሉ የኮምዩኒኬሽን መዋቅር የውሳኔ ሰጪነትና የማስፈጸም አቅምን ለማሳደግ በአደረጃጀት ደረጃ የኮምዩዩኒኬሽን ባለሙያዎች ክፍል፣ የቤተ-መጻሕፍት ባለሙያ ክፍልና የኦዲዮቪዥዋል ባለሙያዎች ክፍል አሉት፡፡ ነገር ግን የተጠሪ ተቋማት፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ የአግሮና ሌሎች ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ የኮምዩኒኬሽን ሥራን ያሳተፈ ተናቦ መሥራት የሚቻልበት መዋቅር ባለመቋቋሙ፣ ወጥ የሆነ መረጃ ለማሕበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ አልተቻለም፡፡
ከዚህም በተጨማሪ እየተሠሩ ያሉ የኮምዩዩኒኬሽን ሥራዎች ውጤታማ የሆነ ስትራቴጂን የተከተሉ ሳይሆን በተለምዷዊ አሠራር ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው፣ እንዲሁም ግልጽነትና ተጠያቂነትን ባሰፈነ መልኩ እየተመሩ ባለመሆኑ ውጤታማነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
በመሆኑም የተቋሙን አጠቃላይ የኮሚዩኒኬሽን ሥራ በውጤታማነት ለመምራት የሚያስችል የኮሚዩኒኬሽን ስትራቴጂ ሰነድ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

# 4. የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂው መነሻዎች

## 4.1. የኢትዮጵያ ታምርት የንቅናቄ እቅድ እንደ መነሻ

መንግስት የሀገራችንን የኢኮኖሚ መዋቅር ዘላቂነት ባለው ጠንካራ መመሠረት ላይ ለማደላደል ልዩ ልዩ ጥረቶችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ለእቅዱ ስኬትም በሀገር ውስጥ ለግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆኑ ልዩ ልዩ የድጋፍ ፓኬጆችን በመቅረፅ፣ በየወቅቱ የሚነሱ ፍላጎቶችን ታሳቢ ያደረጉ ስትራቴጂዎችን በመቅረፅና የተለያዩ ማበረታቻዎችን በማመቻቸት ዘርፉን ለማሳደግ ጥረት አድርጓል፡፡ ከዚህም በላይ ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸው መሠረተ ልማቶችን በመገንባት ወደትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል፡
ይህም ሆኖ የአምራች ዘርፉ በባህሪው በአንድ ተቋም ብቻ እየተመራ ለውጤት የሚደርስ ባለመሆኑና የበርካታ ተቋማትን የተናበበና የተቀናጀ እንቅስቃሴ የሚሻ በመሆኑ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት አልተቻለም፡ ፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት አንደኛው የኢንዱስትሪ አመራሩ የማስፈፀም ችግር ነው፡፡ ሁለተኛው አሁን ያለው የኢንዱስትሪ አደረጃጀት የተሳለጠ አለመሆንና ኢንዱስትሪውን ለመምራት በሚያስችለው ቁመና ላይ አለመሆኑ ነው፡፡ ሶስተኛው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተናበውና ተቀናጅተው ያለመስራት ችግር ሲሆን ይህም ከእቅድ ዝግጅት እስከአፈፃፀም፣ ከድጋፍ ፓኬጅ ትግበራ እስከመረጃ ፍሰት ድረስ ያልተዋሀደ አሠራር በመስፈኑ በዘርፉ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት አልተቻለም፡፡
በመሆኑም በዘርፉ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት፣ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳታፊ ለማድረግ፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን እርስበእርስ ተሳስረው እንዲያድጉና ለታላላቅ አምራች ኢንዱስትሪዎች መሠረት እንዲሆኑ ብሎም ደረጃ በደረጃ በኢኮኖሚው መዋቅራዊ ሽግግር እንዲያመጡ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ታምርት የንቅናቄ እቅድ ተዘጋጅቶ ወደትግበራ ገብቷል፡፡

ይህን እውን ለማድረግም የኮሙኒኬሽን ስራው ራሱን ችሎ ሚናውን እንዲወጣ ለማስቻል ስትራቴጂው ተገቢው ቦታ ሠጥቶታል፡፡ ከዚህ አንፃር ስራዎችን በታለመላቸው የስኬት ልኬቶች ማከናወን እንዲቻል ለማገዝ፣ የተበታተነውን የዘርፉን የኮምዩኒኬሽን እምቅ አቅም ለማስተባበርና ወጥነት ባለው አሠራር ለማገዝ እንዲቻል ይህ ስትራቴጂ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

## 4.2. የአምራች ኢንዱስትሪ ረቂቅ ፖሊሲ

የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማሳደግና ኢኮኖሚያዊና መዋቅራዊ ሽግግሩን ለማሳካት ዘመኑን በዋጀ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መምራት በማስፈለጉ አዲስ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል፡፡
ፖሊሲው በዋናነት ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ወሳኝ የትኩረት አቅጣጫዎች በመለየትና የአፈፃፀም ስልቶችን በማመላከት በዘርፉ ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡
አዲሱ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ በዋናነት በሰባት መሠረታዊ ጉዳዮች ዙርያ ማሻሻያዎችን አድርጎ የማስፈፀሚያ ዝርዝር ስልቶችን አስቀምጧል፡፡ እነዚህም ማሻሻያዎች ለአምራች ኢንዱስትሪ የተመቻቸ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ መፍጠር፣ ምቹ የቢዝነስ ምህዳር መፍጠር፣ የተሻሻለ ፋይናንስ አቅርቦት፣ ክህሎትና ስራ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን፣ ምርት ልማትና ተወዳዳሪነት እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ለማሳካት በኮምዩኒኬሽን ስራዎች የታገዘ እንቅስቃሴ ወሳኝ ነው፡፡ በዚህ መነሻነትም ስራውን በኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ደረጃ መመራቱ ለፖሊሲው ውጤታማነት ያለው ሚና በመታመኑ ሠነዱ መነሻ ሆኗል፡፡

## 4.3. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ እንደመነሻ

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መሪ የልማት እቅድ በዋናነት ከ2013 — 2022 ዓ.ም የኢንዱስትሪ ዘርፉን ትስስር ለማጠናከር፣ በባለሀብቶች የጎላ ተሳትፎ የበለፀገች ሀገርን ለመገንባት፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚን እውን ለማድረግና አጠቃላይ የኢኮኖሚ ምርታማነትን ለማሳደግ የተዘጋጀ ነው። የዕቅዱ አላማዎች በዋናነት ነባርና አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ምርትና ምርታማነት እንዲጨምሩ፣ ከዘላቂ የአካባቢ ልማት ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑና በዘርፉ የስራ ፈጠራ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ማስቻል፣ እንዲሁም በአሴት ጭማሪ የላቁ የውጭ ንግድ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት በማሳደግ የውጪ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ ናቸው። ለኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ አቅም መሠረት መጣል፣ የስራ ዕድል መፍጠር፣ የገቢ ንግድን (ምርትን) መተካትና የውጪ ምንዛሬን ማስገኘት በዕቅዱ ዓላማዎች መነሻነት የተያዙ ዋና ዋና ሚናዎች ናቸው።
በመሪ የዓስር ዓመት ዕቅዱ የተያዙ ሀገራዊ ተልዕኮዎችን በኮምዩኒኬሽን ተግባራት በማጀብ በሚፈለገው ልክ ለማሳካትና የኮምዩኒኬሽን ስራውንም በዘላቂ አሠራር ለማከናወንና በዕውቀት ለመምራት የሚያስችለውን ይህንን ስትራቴጂ ለማዘጋጀት እንደመነሻ ተወስዷል።

## 4.4. የዓለም አቀፍ እና ሀገር ውስጥ የተቋማት የአምራች ዘርፉ የኮሙኒኬሽን ሥራዎች ተሞክሮ

በሀገር ውስጥ ተሞክሮ ምልከታችን ምንም እንኳን በኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ደረጃ የዳበረና የተጠናቀቀ የተቋማት ስትራቴጂክ ሰነድ በተፈለገው መጠን ባይገኝም በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁትን የትምህርት ሚኒስቴር፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የቀድሞውን የከተማ ልማትና ቤቶች ልማት ሚኒስቴርና የቀድሞውን የፕላንና ልማት ኮሚሽንን የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ሠነዶች ለማየት ጥረት ተደርጓል። እነዚህ ሠነዶች ምን ያህል ተግባራዊ ሆነው ምን አይነት ለውጥ አመጡ የሚለውን ለመፈተሽ የተደረጉ ሙከራዎች አልተሳኩም።

ከዚህም ባሻገር ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የ10 ዓመት ፍኖተ ካርታ እቅድ፣ ከመንግስት ኮሙኒኬሽን ረቂቅ ስትራቴጂና ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣ ልዩ ልዩ በህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ላይ ከሚያጠነጥኑ መጻሕፍት፣ መጣጥፎችን፣ የጥናት ሠነዶች እንዲሁም ከልዩ ልዩ ድረገጾች የተገኙ ጉዳዮች ለስትራቴጂክ ሠነዱ ዝግጅት ግብዓትነት አገልግለዋል።
በአሠራር ሂደቱ ውስን ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥ ስትራቴጂዎች ማግኘት ቢቻልም ከንድፈሐሳብና ከተግባራዊነት አንፃር ከሀገር ውጪ የተገኙ ተሞክሮዎችን እንደዋነኛ ግብዓትነት በመጠቀም ከተቋሙ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

## 4.5. የዓለም አቀፍ ተሞክሮ

የኮርያ፣ የሲንጋፖር፣ የጃፓንና የቦትስዋና ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት ሀገራቱ የአምራች ዘርፉን ለማሳደግ ኮሚኒኬሽንን እንደ ዋና መሳሪያ ተጠቅመዋል።
ሲንጋፖር ፡-እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1980ዎቹ የሩቅ ምስራቋ ሀገር ሲንጋፖር የምርታማነትን አጀንዳ ይዛ ከፍተኛ ንቅናቄን ማድረግ ችላለች። በዚህም ከተራ የወደብ ክልልነት ወደ ታላቅ የማኑፋክቸሪንግ ማዕከልነት ለመሸጋገር ችላለች። ሲንጋፖር ለዚህ ስኬት የበቃችው ማላመድን፣ ማሸጋገርንና ዓለማቀፋዊ

ገፅታ ማላበስን በተከተለ የኮምዩዩኒኬሽን ስልት ነበር፡፡ በዚህም እ. አ. አ በ1963 553 ዶላር የነበረውን የሀገሪቱ የዜጎች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2009 ወደ 37 ሺህ 220 ዶላር ለማሳደግ ችላለች፡፡

ሲንጋፖር ለዚህ የምርታማነት ንቅናቄ ስኬት ከተጠቀመችባቸው ባለሶስት ደረጃ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ቀዳሚው የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ነው፡፡ ለዚህም ስኬት የኮምዩኒኬሽንን አቅም ህዝብን ለማስተማር፣ ለመረጃ ስርጭትና ስልጠና፣ የተቋማትን ብራንድ ለማጠናከር፣ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተሻለ መግባባት ለመፍጠርና ምርታማነትን በስፋት ለግሉ ዘርፍ ለማስተዋወቅ ተጠቅመውበታል፡፡
ጃፓንም፡- በተመሳሳይ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከደረሰባት ድቀት ለማገገምና ኢኮኖሚዋን ለማሻሻል ማኑፋክቸሪንግን እንደዋነኛ መዳኛ የቆጠረች ሀገር ነበረች፡፡ በወቅቱ የጃፓን የአምራችነት አቅም ከአሜሪካ በ1/9ኛ ያነሰ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህንኑ እውነታ ለመቀየር የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች አምራች ዘርፉን በማስተዋወቅ፣ በኢንዱስትሪ ዘርፉና ትምህርት ተቋማት መካከል በጋራ የመሥራት ሁኔታን በማመቻቸት ረገድ ከፍተኛ ጥቅም ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ተቋማት አሠራራቸውን እንዲያዘምኑና እንዲሻሻሉ በማድረግ በኩል ውጤታማ ሥራዎችን ለመሥራት ችሏል፡፡ በዚህ ሂደትም የዛሬዋን ጃፓን ባለጠንካራ ኢኮኖሚና ግዙፍ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ባለቤት ለማድረግ ተችሏል፡፡

ቦትስዋና ፡- ከአፍሪካ ሀገራት መካከል ቦትስዋና የብሔራዊ ምርታማነት ንቅናቄን በሲንጋፖር ድጋፍ የጀመረች ሲሆን፤ በብሔራዊ ምርታማነት ማዕከል በኩል ህብረተሰቡን በምርታማነት ላይ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ ሚኒስትሮችን፣ የፓርላማ አባላትንና ዋና ሥራ አስፈፃሚዎችን ጨምሮ ለመንግስትና ለግሉ ሴክተሮች ተከታታይ ምርታማነት ላይ ያተኮሩ ሴሚናሮች በማካሄድ እንዲሁም "የምርታማነት ሳምንት" ንቅናቄ በመሰየም ወደ ተግባር ገብተውም ነበር ፡፡
ይሁን እንጂ የምርታማነት ንቅናቄው በከፍተኛ የአመራር ቁርጠኝነት የተጀመረ ቢሆንም ንቅናቄውን ዘላቂና የራስ ለማድረግ የተሠሩ ሥራዎች አናሳ መሆን፤ ከግንዛቤ ያለፈ የተግባር ሥራዎች ውስን በመሆናቸው ተጨባጭ ውጤት ማስመዝገብ አልቻሉም፡፡

የኮሪያ ፡- 1970ዎቹ ኮርያ ስፋት ያለውን የሱ ንቅናቄ (Saemaul Movement) የልማት ንቅናቄ አካሂዳለች፣ በዚህም በድህነት ቅነሳ፣ በመሠረተልማት ተደራሽነት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በባሕል ሽግግርና አምራችነት እንዲሁም በወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ችላለች፡፡
በኮሪያ የንቅናቄ ዋና ዓላማው የነበረው የገጠር መንደሮችን ወደ ከተሜነት መቀየርና የህዝብ ኑሮን የማሻሻል አካሄድ ሲሆን፤ ለሀገሪቱ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ግንባታና የአምራች ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪነት የራሱን አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡ በንቅናቄው ጠንካራ የተግባቦት ሥራ መሰራትና ይህም የሁሉንም ማህበረሰብ የነቃ ተሳትፎና አካታችነት የተከተለ በመሆኑ ብሔራዊ መተማመንን የገነባ፣ የ"ይቻላል" መንፈስን ያሳደገና ጊዜ ተሻጋሪ የጋራ ራዕይ በመቅረጽ በማሕበረሰብ ደረጃ የአስተሳሰብ ለውጥ ያመጣ ንቅናቄ ነበር፡፡

የተጠቀሱት ሀገራት ኮምዩኒኬሽንን ተጠቅመው ውጤታማ በመሆናቸውና ግንዛቤ ከመፍጠር ያለፈ የተግባር ሥራ በመሥራት ውጤታማ የሆኑበትንና እንዲሁም ጠንካራ የኮምዩኒኬሽን ሥራ ባለመሥራታቸው የገጠማቸውን የውድቀት ሂደታቸውን ለስትራቴጂው ዝግጅት እንደመነሻ ተጠቅመናል፡፡
ከሀገራቱ የወሰድናቸው ኮምዩኒኬሽን ተኮር ተሞክሮዎች እንደሚከተለው ጠቅለል ተደርገው ቀርበዋል፡፡

* ከሲንጋፖር፡- የወሰድንነው ተሞክሮ በዘርፉ ውጤታማ ከሆኑ ሐገራት ያገኟቸውን ተሞክሮዎች በውጤታማነት ወደሐገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ የቀየሩበት ስኬታማ መንገድ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህንኑ የምርታማነት እቅስቃሴ ውጤታማ ለማድረግ ለኮሚዩኒኬሽን ስራዎቻቸው ቅደም ተከተል በመስጠት ማከናወናቸውን ወስደናል፡፡

በተጨማሪም ኢንዱስትሪ፣ ሠራተኛና አመራሩ የጋራ የምክክር መድረክ እንዲኖራቸው፣ በንቅናቄው እና በአምራች ዘርፉ ዙሪያ በቂ ስልጠና ማከናወናቸው፣ ለሠራተኞች ውጤት ተኮር ማበረታቻዎች (ቦነስ) ማመቻቸታቸው፣ ለረጅም ጊዜ ለሚያገለግሉ ሠራተኞች ልዩ ሽልማት የመስጠት ባሕልን መትከላቸው እንዲሁም ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራዎች ወድድር ማዘጋጀት መቻላቸው በውስጥም ሆነ በውጪ የኮምኒኬሽን ሥራ ውጤታማ ስላደረጋቸው እንደልምድ ተወስዷል።

* ከጃፓን ፦ በዘርፉ ካደጉ ሐገራት ያመጡትን ተሞክሮ ወደ ሀገራቸው ለማላመድ ርቀትና ይህም እንዲሳካ ኮሚዩኒኬሽን ትልቁን እገዛ ማድረጉ፤ ከንቅናቄው ጋርና ከአምራች ዘርፉ አስፈላጊነት አንጻር የተሠሩ የግንዛቤ ሥራዎችን ውጤታማነት ወስደናል፡፡

* ከቦትስዋና፡- የምርታማነት ሳምንትን የመሳሰሉ ሁነት ዝግጅቶችንና የኮምዩኒኬሽን ስልቶችን እንደመልካም ተሞክሮ፣ እንዲሁም የኮምዩኒኬሽን ስራዎች በተግባር ስራዎች ካልተደገፉ የሚያመጡትን ውድቀት እንደአሉታዊ ተሞክሮ ወስደናል።

* ከኮሪያ፡- የወሰድነው ተሞክሮ የጋራ የስኬት መንፈስን ለመፍጠርና በማኅበረሰቡ ዘንድ የአመለካካት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የጋራ ውጤታማ ተረክ የማመንጨትና በዚህም የህብረተሰብ የነቃ ተሳትፎና ጠንካራ የተግባቦት ሥራ መሥራትን ወስደናል፡፡

## 4.7. የአምራች ኢንዱስትሪ ምንነትና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማሽንን፣ መሳሪያን ወይም ጉልበትን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው ምርት የሚያመርት ዘርፍ ነው። አምራች ኢንዱስትሪ በጥሬ ዕቃዎችና ሸቀጦች ላይ በሰው ጉልበት፣ በማሽነሪዎችና በኬሚካል ማቀነባበሪያዎች በመጠቀምና እሴት በመፍጠር አዳዲስ ምርቶችን የማምረት፣ የማቀነባበር ወይም የማዘጋጀት የምርትና የንግድ ሂደት ሲሆን፤ ይህም ሁሉንም የምግብና መጠጥ ምርቶች፣ ኬሚካሎች፣ ጨርቃጨርቅ፣ ማሽኖችና መሳሪያዎች፣ ከተመረቱ ማዕድናት የሚመነጩ የተጣሩ ብረቶችና የእንጨትና የእንጨት ውጤቶችን …ወዘተ ያካትታል።

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 በተደረገው ሀገራዊ የተቋማት አወቃቃር መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችንና ሕጎችን ማመንጨት፣ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳና የምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪዎችና የመሳሰሉት ንዑስ ዘርፎች እምቅ አቅምን ማውጣት፣ በዘርፉ ምርምርና ጥናት የሚያካሂዱ ማዕከላት መደገፍና ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመር፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤ ከሚመለከተው ዘርፍና አካላት ጋር በመቀናጀት የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ማድረግንና የመሳሰሉ ተግባራትን እዲያከናውን ሓፊነት ተሠትቶታል።

ከዚህም በተጨማሪ ገቢ ምርቶችን መተካት፣ የውጪ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ፣ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠርና ችግር ፈቺ ምርምር ማካሄድ ላይ አተኩሮ ይሠራል።

የሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራቸው ስድስት ማዕከላትን የያዙ ሶስት ተጠሪ ተቋማት አሉት ። ስለሆነም ተቋሙን በሚኒስቴር መስሪያ ቤት፣ በከተማ አስተዳደርና በክልል ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ለተገልጋዮች መረጃና ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል።

## 5. የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂው ግብ

የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል የውስጥና የውጪ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ፣ ወጥነትና ቀጣይነት ያለው የኮምዩኒኬሽን ሥራዎችን በማከናወን፣ ግንዛቤን የመፍጠር፣ የአመለካከት ለውጥን የማምጣትና የባህል ሽግግርን እውን በማድረግ ዜጎች የዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለሚሠራው ሥራ አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው።

## 6. የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂው ዓላማ

የተቋሙን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ ግብ ለማሳካት የሚያስችሉ ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተለዋዋጭና ሁሉን አቀፍ የውስጥና የውጭ የኮምዩኒኬሽን ስልቶችን በመጠቀም ዘርፉን ማስተዋወቅ፣ የተቋሙን ገጽታ መገንባትና የጋራ መግባባትን መፍጠርና ማሳደግ ነው።

## ዝርዝር ዓላማዎች

- ለኢንደስትሪ ዘርፍ ተዋንያን በተቋሙ ግቦች፣ ዓላማ፣ ራዕይና ተልዕኮ አፈጻጸም ላይ ያተኮረ መረጃ በማሰራጨት ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤
- ከሀገር ውስጥና ከውጭ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የኢንደስትሪ ዘርፉን መረጃ ተደራሽነት አማራጮችን ማስፋት፤
- ከተጠሪ ተቋማት፣ ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች የኢንደስትሪ ቢሮዎች ጋር ጠንካራና ስኬታማ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ማድረግ፤
- የኢንደስትሪ ዘርፍ መሪ እቅድ (ስትራቴጂ) ለማሳካት የዕለት ተዕለት የሥራ ግንኙነት ካላቸው ተቋማት መካከል የጋራ ጥረትን የሚያጎለብት የኮምዩኒኬሽን አቅምና የሥራ ግንኙነት ማስፈን፤
- ከአግሮና ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ከአምራች ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራና የተቀናጀ የኮሚዩኒኬሽን ሥርዓት መፍጠር፤
- በተቋሙ ውስጥ ጠንካራ የውስጥ ግንኙነት በመገንባትና ዘርፈ ብዙ የግንኙነት ሥርዓት በማስፈን የአመራር አባላትና ሠራተኞች ለጋራ ዓላማ እንዲሠሩ የሚያስችሉ የኮሚዩኒኬሽን ተግባራትን መፈጸም፤
- የተቋሙን መለያ (ብራንዲንግ) ማስተዋወቅና ማስረጽ፤
- ቋሚና ወቅታዊ የሚዲያ ፕሮግራሞችና የህዝብ ግንኑነት መንገዶች እንዲኖሩ ማድረግ፤
- የተቋሙ የኮምዩኒኬሽን ሥርዓት የሚመራባቸው መመሪያዎች እንዲኖሩና ተፈጻሚ እንዲሆን ማስቻል፤
- የቢዝነስ ጋዜጠኝነት ለኢንደስትሪ ዘርፍ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ስትራቴጂያዊ ድጋፍ መስጠትና አቅማቸውን ለመገንባት የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤
- ቀውሶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የኮሚኒኬሽን ሥራ መሥራት
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ማሕበራዊ ኃላፊነትና ባለ ብዙ ዘርፍ አሠራሮችን ማጠናከርና ተቋማዊ ገጽታን መገንባት፣
- አካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መረጃ እንዲደርሳቸው ማድረግና በኢንዱስትሪ ዘርፍ የባለድርሻ አካልነት ተሳትፏቸውን ማጎልበት፤
- የዘርፉ መረጃዎች ብዝኃነትን ባማከለ መንገድ ተደራሽ እንዲሆኑ በተለያዩ ቋንቋዎች ማሰራጨት፤



# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን የነባራዊ ሁኔታ ትንተና

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የውስጥና የውጪ ኮምዩኒኬሽን ትንተና ካደረገ በኋላ የህዝብ ግንኙነትና ኮምዩኒኬሽን ሥራዎች እንደተቋም ጠንካራና ደካማ ጎኖችን፣ መልካም አጋጣሚና ስጋቶችን የለየ ሲሆን፤ ጠንካራ ጎኖቹን የበለጠ ለማጠናከር፣ ደካማ ጎኖቹን ለማሻሻል በትንተናው የተለዩ መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም ኮምዩኒኬሽኑን ማሳለጥ እንዲሁም ስጋቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ወደፊት ሊከሰት የሚችል ፈተና አስቀድሞ በማቀድ ማስተዳደር ይገባል። ለዚህም የተለዩት ዋና ዋና ጉዳዮች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### ሰንጠረዥ 1. የጠንካራ እና ደካማ ጎኖች የSWOT ትንተና 2015

| ጠንካራ ጎኖች | ደካማ ጎኖች |
|---|---|
| • የበላይ አመራሩ ለኮሚኒኬሽን ሥራዎች ያለው ድጋፍ፣<br>• ማኅበራዊ ሚዲያውን ለመጠቀም ሙከራዎች መኖራቸው፤<br>• ተቋሙ ከሜንስትሪም ሚዲያው ጋር ለመሥራት ያለው ተነሳሽነት ጥሩ መሆኑ፤<br>• ሁሉንም ሚዲያዎች ማሳተፉ፤<br>• ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች ጋር መልካም የሥራ ግንኙነት መኖሩ፤<br>• ተቋሙ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገው እንቅስቃሴ መኖሩ፤<br>• የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መሻሻል እና ሕጋዊ ማእቀፎች (ደንብ፣ ስትራቴጂና መመሪያዎች ወ.ዘ.ተ.) መዘጋጀታቸው<br>• በሙያው ልምድና ዕውቀት ያላቸው የሥራ ኃላፊዎችና ውስን ባለሙያዎች መኖር፤<br>• የሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማመቻቸቱ | • የተቋሙ ሠራተኞች በኮምዩኒኬሽን ሥራዎችና ጠቀሜታቸው ዙርያ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑ እና ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ መሆን፤<br>• የውስጥ ግንኙነት አግባብ በቴክኖሎጂ ሥርዓት አለመመራቱና አለመደገፉ፣<br>• የተሟላ የአምራች ኢንዱስትሪዎች መረጃ ቋት አለመኖር፤<br>• ማዕከላዊ የመረጃ ፍሰት የአሠራር ሥርዓትና ስትራቴጂ አለመኖር፤<br>• በታቀደው መሰረት የክትትል፣ የግብረ መልስ ሥርዓት አለመኖር፤<br>• የማኅበራዊ ሚዲያ ተደራሽነት አናሳ መሆን፤<br>• በስትራቴጂ፣ በደንብ እና መመሪያ መሰረት የሚመራ የኮሚኒኬሽን አሠራር ሥርዓት አለመኖር<br>• የሚዲያ ግንኙነቱ ወጥነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ አለመተግበሩ፤<br>• የሚዲያ ሞኒተሪነግ ውስንነት መኖር<br>• የተቋሙ መካከለኛ አመራሮችና ሥራቸውን በኮሙኒኬሽን ያለማስደገፍ፣<br>• የተቋሙ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ወቅታዊና ተቋማዊ መረጃዎችን በማሠራጨት የተቋሙ ልሳን በመሆን እንቅስቃሴ ላይ ደካማ መሆን፣<br>• ከተመረጡ ሚዲያዎች ጋር ቋሚ የቴሌቪዥንና ሬዲዮ የአየር ሰዓት ገዝቶ አለመሥራት<br>• ዓለማቀፍ ሚዲያውንና የሀገር ውስጥ የቋንቋ ብዝሐነት ታሳቢ ያደረጉ የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች አናሳ መሆን<br>• የሥራ ክፍሉ መዋቅር ለመረጃ የሚመችና፣አሳታፊ እና በቂ ቁሳቁስ የተሟላ አለመሆን፣የባለሙያዎች አቅም ክፍተት<br>• የሥራ ክፍሉ የከፍተኛ ሥራ አመራር አባል ባለመሆኑ የሚሰጥውን አቅጣጫ እና ውሳኔ ለመተግበር ውስንነት መኖር፤<br>• የሚዲያ ፎረም አለመቋቋም |

## ሰንጠረዥ 2. መልካም አጋጣሚና ስጋት የSWOT ትንተና 2015

| መልካም አጋጣሚ | ስጋት |
|---|---|
| • መንግስት ለህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽንና ልዩ ትኩረት መስጠቱ፤<br>• ሁሉም የመንግስት አመራር በተመሳሳይ/ ተመጋጋቢ ፍሬሚኒግ ኮሙኒኬት ማድረግ እንዳለበት ከመንግሥት አቅጣጫ መቀመጡ፤<br>• ሀገራዊ ውጤታማ የሆነ ጠንካራ የኮሙኒኬሽን አደረጃጀትና መዋቅር እየተዘረጋ መሆኑ፤<br>• የተባበሩት መንግስታት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረትና የኢንዱስትሪ ሳምንት እንዲከበር መወሰኑ<br>• ጠያቂ ማሕበረሰብ መፈጠሩ፤<br>• ለአምራች ኢንዱስትሪው ምቹ የሆኑ መሰረተ ልማቶች መስፋፋት፤<br>• የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ፕላትፎርሞች ዕድገት እየጨመረ መምጣት፤<br>• በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ መጀመሩ<br>• ሀገር አቀፍ የኮሙኒኬሽን ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ ሊደረግ መሆኑ፤<br>• የልማት አጋር ድርጅቶችና ሕብረተሰቡ የኢንዱስትሪና ኮሙኒኬሽን ዘርፉን ለመደገፍ ፍላጎት መኖር<br>• የሀገሪቱ ሚዲያዎች ለዘርፉ ትኩረት ሰጥተው እየሠሩ መሆኑ፤<br>• የማህበረሰብና ባለድርሻ አካላት በአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ፍላጎት መኖር፤ | • በየአካባቢው ያሉ የጸጥታ ችግሮች<br>• ሚዲያዎች ለዘርፉ የቅድሚያ ትኩረት ያለመስጠት<br>• ድንገተኛ አደጋ<br>• የመንግስት ሚዲያዎች የፕሮዳክሽንና የስርጭት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ<br>• የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ባለሙያዎች ፍልሠት<br>• አምራች ኢንዱስትሪዎች ለሚዲያና ኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች በቂና ወቅታዊ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን<br>• የተጠሪ ተቋማት ለኮሚዩኒኬሽን የሥራ ክፍል በቂና የሚመጥን የሠው ኃይል አደረጃጀት አለመኖሩ<br>• የውጭ ምንዛሬ እጥረት |


904899

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ራዕይ፣ተልዕኮ እና ዕሴቶች

### ራዕይ

በ2022 በስኬታማ ኮሚዩኒኬሽን ታግዞ የባለድርሻ አካላትንና የሕብረተሰቡን ተሳታፊነትና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ያረጋገጠ የኢንዱስትሪ ዘርፍ እውን ሆኖ ማየት፡፡

### ተልዕኮ

አሳታፊና ተደራሽ የሆነ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ለማሕበረሰቡና ለባለድርሻ አካላት በማድረስ የጋራ መግባባትን በመፍጠርና በማሳደግ የተቋሙን ገጽታ መገንባት ነው፡፡
የስትራቴጂው እሴቶች

- መታየት /Visibility/
- ወጥነት /Consistency/
- ግልፅነት/Transparency/
- ተደራሽነት /Accesebility/
- ትክክለኛነት /Accuracy/

## 3.1 የስትራቴጂው መርሆዎች

### ተቋሙና ኮምዩኒኬሽን

ኮምዩኒኬሽንና ተቋሙ ተነጣጥለው ሊታዩ አይችሉም፡፡ ለአንድ ዘመናዊ ተቋም ኮምዩኒኬሽን ህልውናው ነው፡፡ ኮሚዩኒኬሽን መረጃዎች የሚተላለፍበት መንገድ ብቻ ሳይሆን ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ አዳዲስ አስተሳሰቦች የሚገነቡበት እንዲሁም በሚፈጠሩ ጠንካራ ግንኙነቶች አማካኝነት የውስጥ አመራርና ሠራተኞች ለጋራ ዓላማ በትብብር እንዲሠሩ የሚደረግበትና ሁሉንም ባለድርሻ አካላትና አጋሮች አንድ ላይ ለማስተሳሰር የሚረዳ የተቋሙ ወሳኝ የህልውናው አካል ተደርጎ ተወስዷል፡፡
የተመጣጠነ የውስጥና የውጭ ምልከታ
የተቋሙን ሠራተኞች ልብ የማግኘትና መልካም የሥራ ባህልን የመገንባት ሂደት በተቋሙ ውስጥ በሁሉም አቅጣጫዎች በሚደረጉ መረጃ ልውውጦችና ግንኙቶች ዓይነት ይወሰናል፡፡ በመሆኑም የውስጥ ኮምዩኒኬሽን ዘርፍ ትኩረትን ይሻል፡፡ በሌላ በኩል ተቋሙ የተሰጠውን አገራዊ ተልዕኮ በብቃት ሊወጣ የሚችለው ከባለድርሻ አካላትና አጋሮች ጋር በሚፈጥራቸው ስኬታማ ትብብሮችና ሕብረተሰቡን በማስገንዘብና ለተግባር በማነሳሳት ስለሆነ ይህንን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችለው የውጭው ኮሚዩኒኬሽንም በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

## የመረጃዎች ባህሪያት

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እያደራጀ የሚያሰራጫቸው መረጃዎች ቀድመው የታቀዱ፣ ወጥነት ያላቸው፣ ከመሰራጨታቸው በፊት ተፈትነው ትክክለኛነታቸውና ለታለመላቸው ተደራሲያን (ባለድርሻ አካላት) ተገቢነታቸው የተረጋገጠ፣ አመለካከትን የመሞገት ጉልበት ያላቸው ወጪ ቆጣቢና ፈርጀ ብዙ የአቀራረብ ስልቶችን የሚከተሉ ሊሆን ይገባል፡፡

የተተኮረባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችና ባለድርሻ አካላት

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አመንጭቶም ይሁን አሰባስቦ የሚያሰራጫቸው መረጃዎች ያለ ገደብ ለሁሉም ዜጎችና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡ ይሁንና የትኛውም የኮምዩኒኬሽን ተግባር ትኩረት የሚያደርግባቸው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከአምራች ኢንዱስትሪው እድገት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ነገር ግን እስከአሁን በዘርፉ የሚጠበቅባቸውን ያህል ተሳትፎ በማድረግ ላይ ያልሆኑትን አካላት ነው፡፡

የሕዝብ ግንኙነት ሞዴል

ከአማራጭ የሕዝብ ግንኙነት ሞዴሎች ውስጥ ዘርፉ ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግን፤ መረጃ ማሰራጨትን፣ ኅብረተሰቡንና ባለድርሻ አካላትን በማሳመን በአምራች ኢንዱስትሪው ላይ ያላቸውን ተግባራዊ ተሳትፎ ማሳደግንና ከስትራቴጂካዊ አጋሮች ጋር እየተወያዩ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ሐሳብ ማፍለቅን ትኩረታቸው ያደረጉትን ሞዴሎች እንደአግባብነቱ በተናጠልና በቅንጅት በጥቅም ላይ ማዋሉ ተመራጭ እንደሚሆን ታምኖበታል፡፡

## 1. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባለድርሻ አካላት ትንተና

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠብቀው የሥራ ግንኙነት | ባለድርሻ አካላት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ማግኘት የሚፈልጉት አገልግሎት | የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ደረጃ | የኮምዩኒኬሽን መንገድ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የተቋሙ አመራርና ሠራተኞች | የአመራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በበላይነት መምራት፥ አቅጣጫ መስጠት<br>ለዘርፉ ልማት ምቹ ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን መፍጠር፤<br>የመስሪያ ቤቱን ዕቅድ በአግባቡ መገንዘብ ማቀድና በመተግበር ማሳካት፤<br>በሚፈለገው የሥራ መስክ በባለቤትነት መንፈስ መሥራት፣<br>አዳዲስ የፈጠራ ሐሳቦችን ማመንጨት፣<br>የዘርፉ አምባሳደር መሆን፤<br>ከባለድርሻ አካላት ጋር ውጤታማና የቅንጅታዊ አሠራርን መዘርጋት፤ | ለሥራ የሚሆን የፋይናንስና ሎጀስቲክስ አቅርቦት፤<br>ወቅቱን የጠበቀ የአቅም ግንባታ ስልጠና<br>ምቹ የሥራ ሁኔታና የሥራ ማበረታቻ<br>ድጋፍና ክትትል<br>ጠንካራ የቡድን ስሜትና ሐላፊነት ያለው አመራርና ሠራተኛ፤<br>ስልጡን የሰው ሃይል፤<br>ከባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ ውጤታማ አመራር ማግኘት፤ | ከፍተኛ | ወርሀዊና የሩብ ዓመት ስብሰባዎች<br><br>እና<br><br>ሁሉም የኮምዩኒኬሽን መንገዶች |
| 2. | አምራች ኢንዱስትሪዎች/ ኢንተርፕራይዞች | ምርትና ምርታማነታቸውን ማሳደግ፣<br>ተጨማሪ የሥራ እድሎችን መፍጠር፣<br>ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን ተክተው ማምረት፣ የሀገር ውስጥ የገበያ ተደራሽነታቸውን ማስፋት፣<br>በዓለማቀፉ ገበያ ተወዳዳሪ መሆን፣ ለዚህም አስቻይ የማሽነሪ፣ የቴክኖሎጂ፣ የአሠራር ስርዓት ልማት ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሠሩ፣ የምርት ሒደታቸው ከከባቢያዊ ደህንነት ጋር እንዳይጋጭ ማድረግ፣<br>ራሳቸውን ማስተዋወቅ፣ ምርታቸውን መሸጥ፣<br>የምርት ሒደታቸው ከከባቢያዊ ደህንነት ጋር ትስስር ያለው እንዲሆን ማድረግ<br>ራስን በእውቀት መገንባት፣ አቅምን አማጦ መጠቀም፣ ጥራት ያለውና ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ማምረት፤ | (በመሠረተ ልማት) በማምረቻ ቦታ፣ በፋይናንስ፣ በግብዓት፣ በማሽነሪ፣ በውጭ ምንዛሬ፣ በህጋዊ ማዕቀፍ ክፍተቶች በገበያ ትስስር ወዘተ የሚፈጠር አላስፈላጊ ቢሮክራሲን ማስቀረት<br>የሀገር ውስጥ ምርት መጠቀም ላይ በሕብረተሰቡ አመለካከት ላይ ለውጥ የሚያመጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት፤ | ከፍተኛ | ሁሉም የኮምዩኒኬሽን መንገዶች |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3. | ተጠሪ ተቋማትና የክልል የዘርፉ አደረጃጀቶች | ለዘርፉ ስኬት አዳዲስ የፈጠራ ሐሳቦችን ማመንጨት፣ ዓለማቀፋዊ ተሞክሮዎችን መቀመርና ማላመድ፤<br>ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ፤<br>የዘርፉን ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎችን ማደራጀት፤<br>የተቋሙን የህዝብ ግንኙነትና ኮምዩኒኬሽን ማጠናከር፤<br>የአካባቢና ዓለማቀፍ የገበያ መዳረሻን ማፈላለግ፤<br>የክልሉን የኢንዱስትሪ ጸጋዎች ማስተዋወቅ፤<br>የልምድ ልውውጥ ማካሄድ፤<br>የባለሙያዎችን አቅም መገንባት | የዕውቀትና ክህሎት ድጋፍ ማግኘት፤<br>ወቅቱን የተጠበቀ ግምገማና ግብረመልስ፤<br>የቅንጅታዊ አሰራሮችን መፍጠር ወጥ የመረጃ ማዕከልን ማቋቋም፤<br>ጠንካራ የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን አሠራርን መዘርጋት፤<br>ለዘርፉ ልማት ወሳኝ የሆኑ ደንብና መመሪያዎችን የድጋፍ ማዕቀፎችንና መሰል አስቻይ ሁኔታዎችን ማዘጋጀትና ማጽደቅ፤ | ከፍተኛ | ሁሉም የኮምዩኒኬሽን መንገዶች |
| 4. | ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ተቋማት | ለአምራች ዘርፉ እድገት አስፈላጊ የፋይናንስ አቅርቦትን ማመቻቸት፤<br>የልማት አጋራትን አቅም በማሰባሰብ የዘርፉ ልማት በቴክኖሎጂ፣ በማሽነሪ አቅም፣ በጥናትና ምርምር፣ በስልጠናና በልምድ ልውውጥ የሚዳብርበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤<br>ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስ እፎይታ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ማድረግ፤<br>አዳዲስና ወቅቱን የዋጁ የማበረታቻ ስርዓቶችን መተግበር፤<br>የኢንዱስትሪዎች የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻ እንዲያድግ አስፈላጊ የልዩ ድጋፍ አሠራሮችን መዘርጋት፤<br>የፖሊሲና የጥናት ምርምር ድጋፍ ማድረግ፤ | የሚደረጉ ድጋፎች በትክክል እንዲተገበሩ ማድረግ፣<br>የሀገር ውስጥ አምራቾችንና ምርታቸውን በአግባቡ እንዲተዋወቅ ማድረግ፤<br>የምርትና ምርታማነት አቅማቸው፣ የጥራት ደረጃቸው የዋጋ ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር መረባረብ፤<br>ጥራት ላይ የማይደራደር፣ የገቢ ምርቶችን ታሳቢ ያደረገና የዓለም ገበያውን ያለመ ጠንካራ አምራች እንዲፈጠር ግፊትና እገዛ ማድረግ፤<br>ዘርፉን ሊያሳድግ የሚችል ተገቢና ጥራት ያለው ዕቅድ ማቀድ፤ | ከፍተኛ | ሁሉም የኮምዩኒኬሽን መንገዶች |
| 5. | የመሠረተ ልማት፣ የሳይንስና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ዘርፍ | አምራች ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲዘልቅ የሚያደርጉ ዘመኑን የዋጁ መሠረተ ልማቶችን ተደራሽ በሆነ አግባብ መዘርጋት፤<br>ለኦንላይን የኢንዱስትሪ ምርቶች ሽያጭ መቀላጠፍ የሚረዱ የኢንተርኔት ግብይት ተቋማት እንዲበራከቱ ለማድረግ የሚያስችል ፈቃድና ድጋፍ መስጠት፤<br>በመሠረተ ልማት ግንባታ ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪው አስፈላጊ ቁሳቁሶችን እንዲያመርት በማስቻል የገበያ ተጠቃሚነታቸውን ማስፋፋት፤<br>ሀገር-በቀል ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል የሚረዱ አሠራሮችን፣ ቴክኖሎጂና አስተሳሰቦችን ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ማቅረብ፣ ማላመድና መደገፍ፤<br>የኢንዱስትሪዎችን የምርት ግብይት፣ ማስተዋወቅና የስርጭት አሠራሮችን ከቴክኖሎጂያዊ አቅሞች ጋር በማስተሳሰር ንግድን ማቀላጠፍ፤<br>ወጥ የሆነ የኢንዱስትሪ መረጃ መሠባሰቢያ ቋትና የአሠራር ሥርዓት እንዲፈጠር ድጋፍ ማድረግ፤ | የመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎትን በስፋትና በዓይነት ለማስፋት እንዲቻል የሚረዱ ልዩ ልዩ መረጃዎችን አጠናቅሮ ማቅረብ፤<br>በመሠረተ ልማት አቅርቦት ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን እንዲያመርቱ በማስቻል የተቋሙን የውጭ ምንዛሬ ወጪ መቀነስ፤<br>የጋራ ሥራዎችን የማቀናጃና መገምገሚያ አሠራር ሥርዓትን መዘርጋት፤<br>የኢንዱስትሪዎችን ነባራዊ አቅም፣ ቀጣይ ፍላጎትና ሀገራዊ ተቋማዊ ተልዕኮ መረጃ፣ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን በጋራ ማከናወን፤<br>ወጥ የሆነ የኢንዱስትሪ መረጃ መሰሰቢያ ቋትና የአሠራር ሥርዓት እንዲፈጠር በጋራ መሥራት፤ | ከፍተኛ | ፓናል ውይይት<br><br>ልዩ ልዩ የምክክር መድረኮች<br><br>በሁሉም የኮሙኒኬሽን መንገዶች |
| 6. | የፍትሕና የዴሞክራሲ ተቋማት | የአምራች ኢንዱስትሪውንና አካባቢያቸውን ሰላም ማስጠበቅ፤<br>ለኢንዱስትሪ ልማት ወሳኝ የሆነውን ሀገራዊ ሠላምና መረጋጋት መፍጠር፤<br>ለሚሊተሪ አስፈላጊ የሆኑ አልባሳትና ምግቦች እንዲሁም ቁሳቁሶችን በሀገር ውስጥ አምራቾች እንዲመረቱ በማድረግ የገበያ ትስስርን ማስፋት፤ ሀገራዊ የምርታማነትን አቅምን ማጎልበት፤ | አምራች ኢንዱስትሪዎች ለሠራዊቱ ግብዓትነት የሚውሉ ምርቶችን በጥራትና በፍጥነት ማምረት፤<br>የአምራች ዘርፉን የሚያዘምኑ የቴክኖሎጂ ሥራዎችን በመሥራት ያለውን አስተዋፅኦ ማጎልበት፤ | ከፍተኛ | የቴሌቪዥንና የራዲዮ ፕሮግራም<br>ልዩ ልዩ መድረኮች |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 7. | የግብርናና የማሕበራዊ ዘርፍ | የግብርና ምርቶችን በቴክኖሎጂ ማዘመን፣<br>የኢንዱስትሪ ግብዓት በምርምር በተደገፈ መንገድ ለአምራች ኢንዱስትሪ ግብኣት የሚሆኑ ምርቶችን በበቂና በጥራት ማምረት፤<br>ልዩ ልዩ የግብርና ማሽነሪ አምራቾች የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ማስቻል፤<br>ለአምራች ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶችን በስፋት እንዲቀርቡ ድጋፍ ማድረግ፤ | ለአምራች ኢንዱስትሪው የሚያስፈልጉ የግብርና ግብአቶችን መለየትና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ማቅረብ፤<br>ግብርናውን የሚያዘምኑ ቀላል ማሽነሪዎችን በስፋት በማምረት ለዘርፉ እድገት ወሳኝ ሚና መጫወት፤<br>ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚውሉ የግብርና ውጤቶች በሀገር ውስጥ አምራቾች ገበያ እንዲያገኙ የመረጃና የገበያ ትስስር ሥራዎችን በጋራ መሥራት፤ | ከፍተኛ | ሁሉንም አይነት የኮሙኒኬሽን መንገዶች፣ |
| 8. | የመንግስት ኮሙኒኬሽንና የሚዲያ ተቋማት | ዘርፉ ትኩርት እንዲያገኝና ማሕበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው አጀንዳ አድርጎ መሥራት፤ ለመገናኛ ብዙሀን አቅጣጫ መስጠት፤<br>ዘርፉ ለኢኮኖሚያዊ ሽግግሩ ያለውን ፋይዳ ለማሕበረሰቡ ማስገንዘብ፤<br>ሚ/መ/ቤቱ መገናኛ ብዙሀን ሲጋብዝ በመገኘት ተገቢውን የዘገባ ሽፋን መስጠት፤<br>ተከታታይነት ያለው ፕሮግራም፣ ዜናና ውይይት በመሥራት የመስክ ጉብኝት በማድረግ መረጃ በማጠናቀር ለማሕበረሰቡ በማድረስ ዘርፉን ማሳደግ፤ | ስለ አምራች ኢንዱስትሪ ትክክለኛ መረጃ በየወቅቱ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤<br>ዘርፉን የሚያስተዋውቅበት ቋሚ የአየር ሰዓት መግዛት፤<br>የሚዲያ የመስክ ጉብኝት ማዘጋጀት፤<br>ማህበራዊ ድረ ገጽን በደንብ መጠቀምና ማዘመን፤ | ከፍተኛ | ሁሉንም አይነት የኮሙኒኬሽን መንገዶች፣ |
| 9. | የሙያና የዘርፍ ማኅበራት | ዘርፉን የሚያሳድጉ የምርምር ሥራዎችን መሥራትና መተንተን የሀገር ውስጥ ምርት መጠቀም ላይ ሳይንሳዊ ማብራሪያ መስጠት፣<br>ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂና መመሪያዎችን በመተቸት፣ ጥናታዊ ፅሁፎችን ማቅረብ፤<br>የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋትና የገበያ ትስስር መፍጠር፤<br>የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ማቅረብ፤<br>ስለ ኢንዱስትሪ ዘርፍና ፖሊሲ ለአባሎቻቸው ግንዛቤ መፍጠር፤<br>አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፤<br>ለአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ እድገት በባለቤትነት መንፈስ ሙያዊ አገልግሎት መስጠት፤<br>የአምራች ኢንዱስትሪው የሚያመርተውን ምርት መጠቀም፣ ማስተዋወቅና አምባሳደር ሆኖ ግንዛቤ መፍጠር፤ | ለዘርፉ ሀገራዊ ልማት ምሁራዊ ሚናቸውን መወጣት የሚያስችሏቸው የጥናትና ምርምር ሥራ መሥራት፣<br>የምክክር መድረኮችን ማመቻቸት፤<br>የፖሊሲና የህግ ድጋፍ፤<br>የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋፋት፤<br>አዳዲስ የኢንቬስትመንት አማራጮችን ማመቻቸት፤<br>አቅም ግንባታ፤<br>የማኅበራት የጋራ ፎረም እንዲመሰረት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤<br>የሥራ እድል ማግኘት፤<br>ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲፈጠር ማድረግ፤ | መካከለኛ | ሁሉንም አይነት የኮሙኒኬሽን መንገዶች፣ |
| 10. | የልማት አጋር ድርጅቶች | የበጀት ድጋፍ፤ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የገበያ ማፈላለግ፤<br>የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መደገፍ፤<br>ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሠራር መዘርጋት፤<br>ጥናትና ምርምር ማካሄድ፤<br>የሎጂስቲክና የማሽነሪዎች ድጋፍ መስጠት፤<br>ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ወደ ኢትዮጵያ ማምጣት፤ | የጋራ ስምምነት መፍጠር፤<br>ወቅታዊና የተጠናቀረ የኢንዱስትሪ መረጃ ማግኘት፤<br>ወቅታዊ የፕሮጀክት አፈጻጸም ክትትልና ሪፖርት ማግኘት፤ | ከፍተኛ | G2G, ማህበራዊ ሚዲያ፤ ስብሰባዎችና ሁሉም የኮምዩኒኬሽን መንገዶች |

## የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ግቦች

### 1. ጠንካራና ውጤታማ የውስጥ ኮምዩኒኬሽን መገንባት

የውስጥ ኮምዩኒኬሽን የመስሪያ ቤቱን የበላይና መካከለኛ አመራር አባላትና ሠራተኞች ከላይ ወደታች፣ ከታች ወደላይና በጎንዮሽ የሚያደርጉትን ግንኙነት የሚመለከት፤ ሁሉም ለመሥሪያ ቤቱ ራዕይ፣ ዓላማና ስኬት ተፈጻሚነት በአንድ ልብ ሆነው የሚሠሩበትን የግንኙነት ሥርዓት የመፍጠርና የማስፈጸም ተግባር ነው።

ስለሆነም የውስጥ ባለድርሻ አካላት ኮምዩኒኬሽን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአስር ዓመት መሪ እቅድን ለመተግበር በሚከናወነው ተግባር ውስጥ ለጋራ ዓላማ እንዲሰለፉ፣ የጋራ መግባባት እንዲኖራቸው፣ የሥራ ክፍሎች ተቀናጅተው እንዲሰሩ፣ የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ያደርጋል። በዚህ መሰረት የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ።

- የመሥሪያ ቤቱን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ እቅዶች፣ ስኬቶችና ቁልፍ ተቋማዊ ለውጦችን በየጊዜው ማስገንዘብ፤

- ሠራተኞችን የሚያበረታቱ መርሐ ግብሮችን ማካሄድ፤
- ሁሉም የሥራ ክፍሎች በሥራ ክንውኖች ላይ መረጃ ለመለዋወጥ፤ በእቅድና በአፈጻጸም ላይ ለመወያየት መደበኛ ስብሰባዎችን ማካሄድ፤

- ለሠራተኞች ሥራን የተመለከቱ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን በየጊዜው እንዲያውቁ ማድረግ፤
- መሥሪያ ቤቱን የተመለከቱ ማንኛውም መረጃዎች ሠራተኞች በቀላሉ ኤሌክትሮኒክ በሆነ መንገድ የሚያገኙበትን መንገድ መፍጠር፤
- ሠራተኞች ለበላይና ለመካከለኛ አመራር አባላት በባለቤትነት መንፈስ ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጡ ማበረታታት፤
- በየወቅቱ ዳሠሳዊ ጥናት በማካሄድ ተጨማሪ የውስጣዊ ኮምዩኒኬሽን ተግባራትን ማከናወን፤
- የውስጥ ኮምዩኒኬሽን ኦዲት ማካሄድና ውጤቱን ማሳወቅ፤

### 2.የውጭ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ኮምዩኒኬሽን ማካሄድ

ኢንደስትሪ ሚኒስቴር ካለው የሥራ ባህርይ አንጻር ከመንግሥት ህግ አውጪዎች፣ አስፈጻሚዎችና ተርጓሚዎች አንስቶ እስከ ክልላዊ መንግሥታት የተለያዩ አካላት፤ ከአነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች አንስቶ እስከ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች፤ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሚዲያን ያካተተ ሰፊ የውጭ ባለድርሻ አካላት አሉት። ስለሆነም መ/ቤቱ ለሚያስፈጽመው ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና እቅድ የእነዚህ ባለድርሻ አካላት አጋርነትና ድጋፍ ወሳኝ በመሆኑ ዘላቂነት ያለው ጠንካራ ኮምዩኒኬሽን መገንባት ያስፈልጋል። ይህን ግንኙነት ስትራቴጂያዊ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ።

- የመ/ቤቱ የበላይ አመራሮችና በየደረጃው ያሉ ሐላፊዎች በዘርፉ ያሉ ባለድርሻ አካላትን በየጊዜው ቀርበው እንዲያነጋግሩና የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው ለማድረግ የሚያስችል አሠራርን መዘርጋት
- የኢንደስትሪ ዘርፉን አስመልክቶ በየጊዜው በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች፣ እቅዶች፣ መመሪያዎች ዝግጅት ላይ የባለድርሻ አካላትን አስተያየት መቀበል፤

- በኢንደስትሪ ዘርፍ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትንና የሚያጋጥሙ ችግሮችን በየጊዜው ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ማሳወቅ፤
- በኢንደስትሪዎች መካከል የልምድ ልውውጥና የእውቀት ሽግግር እንዲኖር ማበረታታት፤ አስቻይ ሁኔታዎችንም መፍጠር፤
- የውጭ ባለድርሻ አካላት ያለምንም ውጣውረድ መረጃ የሚያገኙበትን አሠራር ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ማዋል፤
- ስለ "ኢትዮጵያ ታምርት" ንቅናቄ ዓላማና ስኬት ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብሮችን ማካሄድ፤
- የኢትዮጵያን፣ የአፍሪካንና የዓለምን የኢንደስትሪ ቀኖች በጋራ ማክበር፣
- አምራች ኢንዱስትሪን አስመልክቶ የሚከበሩ ልዩ ልዩ በዓላትና የአደባባይ ሁነቶች እንዲኖሩ ማስቻልና አሳታፊ በሆነ መንገድ ማክበር፤
- የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ መስክ ለሚያከናውት ተግባር እንዲረዳ ዘርፉን የተመለከቱ መረጃዎችን በተከታታይ ማቅረብ፤
- የልማት አጋር ለሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማትና የውጭ ባለሀብቶች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በተለያዩ አማራጮችና ቋንቋዎች ማሰራጨት፤
- በዘርፉ የላቀ ውጤት ላመጡ ኢንዱስትሪዎች ዓመታዊ የእውቅናና የማበረታቻ መርሐ ግብሮች ማካሄድ፤
- የውጭ ኮምዩኒኬሽን ኦዲት ማካሄድና ውጤቱን ማሳወቅ፤

## 3.ጠንካራ የሚዲያ ግንኙነት መፍጠር

በኢንደስትሪ ዘርፍ የሚከናወኑት ተግባራት፣ የሚገኙ ስኬቶች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የሚወሰዱ ርምጃዎችን ህዝብ በተለይም በዘርፉ ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት እንዲያውቋቸው ለማድረግ ከአገር ውስጥና ከውጭ የሚዲያ ተቋማት ጋር ዘላቂነት ያለውና በእውቀት ላይ የተመረኮዘ ጠንካራ ግንኙነት ይኖራል፡፡ በዚህ ረገድ የሚከናወኑት ተግባራት ቀጥሎ የተገለጹት ናቸው፡፡

- ጋዜጠኞች ስለ ዘርፉ ወቅታዊ መረጃና መልዕክት የሚያገኙበት የማህበራዊ ሚዲያ መስመር ሥራ ላይ ማዋልና በየጊዜው ወቅታዊ መረጃ መስጠት፤
- በኢንደስትሪ ዘርፍ በየጊዜው ያለውን ለውጥ ለማስገንዘብ በየዓመቱ ለጋዜጠኞች ስልጠና መስጠት፤
- በየጊዜው ተከታታይ መረጃ ለሚዲያ በመስጠት ዘርፉ የማያቋርጥ ሽፋን እንዲያገኝ ማድረግ፤
- ከተመረጡ ሚዲያዎች ዋና አዘጋጆችን በመጋበዝ ከመ/ቤቱ የበላይ አመራር አባላት ጋር ስለ ዘርፉ እንዲወያዩ ማድረግ፤
- ጋዜጠኞች ለሚያቀርቡት ጥያቄ በአፋጣኝ መልስ እንዲያገኙ ማድረግ፤
- በየተወሰነ ጊዜ በቋሚነት ከሚዲያ ተቋማት ተወካዮች ጋር የምክክር ስብሰባ ማካሄድ፤
- ስለ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ በየጊዜው ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት፤
- በኢንደስትሪ ዘርፍ የሚከናወኑትን ተግባራት የሚያስርጹ ትምህርታዊ የሬዲዮና የቴሌቪዥን መርሐ ግብሮችን በተለያዩ ቋንቋዎች ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤
- የኢንደስትሪ ዘርፉን የተመለከቱ ትምህርታዊ ጽሑፎችን በህትመትና በዲጂታል ቅጂዎች በተለያዩ ቋንቋዎች አዘጋጅቶ ማሰራጨት፤
- ውጤታማ የሆኑ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የተመለከተ የሚዲያ ጉብኝት ማዘጋጀት፤

## 4. የተቋሙን የኮምዩኒኬሽን ክፍል አቅም መገንባት

የኢንደስትሪ ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ስራ አስፈጻሚ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ተልዕኮና ስትራቴጂ ለማሳካት እንዲሁም በመ/ቤቱና በተገልጋዮቹ መካከል መስተጋብራዊ ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችል አደረጃጀት፣ የሰው ኃይልና ተቋማዊ አቅም እንዲኖረው ይደረጋል፡፡
ክፍሉ የመ/ቤቱ መገለጫ ሆኖና በቃል አቀባይነት ሚናው በዘላቂነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የበላይ አመራሩ ድጋፍ ይኖረዋል፡፡ ይህ አደረጃጀት ከዘርፉ ተጠሪ ተቋማትና የክልልና የከተማ አስተዳደር የኢንደስትሪ ቢሮዎች የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች ጋር የተናበበ አሠራር በመፍጠር በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የመረጃ ቅብብሎሽ እንዲኖር የሚያስችል ሊሆን ይገባል፡፡ ለዚህም ከዚህ በታች የተገለጹት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

- የሚኒስቴር መ/ቤቱን የኮምዩኒኬሽን ክፍል በአደረጃጀት፣ በሰው ኃይል፣ በቁሳቁስና በተከታታይ ስልጠና አቅማቸውን መገንባት፤

- የተጠሪ ተቋማት፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የኢንደስትሪ ቢሮዎችና የአምራች ኢንዱስትሪዎች የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎችን አቅም በስልጠናና በልምድ ልውውጥ መገንባት፤

- ከተጠሪ ተቋማት፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የኢንደስትሪ ቢሮዎችና የአምራች ኢንዱስሪዎች የህዝብ ግንኙነት ሐላፊዎች ጋር የመረጃ መለዋወጫ መረብ ማዘጋጀት፣ በየጊዜው ውይይት የሚደረግበት መርሃግብር ማካሄድ፤

- ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮምዩኒኬሽን ክፍል አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋል፤
- ለመ/ቤቱ የበላይ አመራርና ለሥራ አመራር አባላት አካባቢያዊ ሁኔታዎችን በመቃኘት የኮምዩኒኬሽን ምክርና አስተያየት መስጠት፤

- ስለ ሚኒስቴር መ/ቤቱና ዘርፉ የተመለከቱ መረጃዎችን የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም በልዩ ልዩ የአገር ውስጥና የውጭ ቋንቋዎች በተከታታይ እያዘጋጁ ማሰራጨት፤

- የመ/ቤቱን ዲጂታል መጽሔት በተከታታይ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤ ተደራሽነቱንም ማስፋት፤
- የመ/ቤቱን ድረገጽና ማህበራዊ ሚዲያዎች ሙያዊ በሆነ መንገድ መምራትና ለዘርፉ ተደራሽና አስተማማኝ የመረጃ ምንጭ እንዲሆን ማድረግ፤

- በኢንዱስትሪ ዘርፍ ግንዛቤን ሊያጎለብቱ፣ የአመለካከት ለውጥ ሊያመጡና የባህል ሽግግር ሊፈጥሩ የሚችሉ መልዕክቶችን በመቅረጽ በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች ማሰራጨት፤

- የቀውስ ጊዜ ኮምዩኒኬሽንን መፈጸም አገራዊ የዘርፉን ገጽታና የመ/ቤቱን መልካም ስም ሊያጎድፉ የሚችሉ ሁኔታዎችን አስቀድሞ መተንበይ፣ ከተከሰተም ከበላይ አመራርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ግልጽነትን በተላበሰ መንገድ ቀውሱን መቋቋም፤ ለህዝብም ወቅታዊ መረጃን ቀዳሚ ሆኖ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የቀውስ ጊዜ ኮምዩኔክሽን በእውቀት የሚመራ ወሳኝ ተግባር በመሆኑ የስትራቴጂያዊ አቅጣጫው አካል ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡-

- ምን አይነት ቀውስ ሊመጣ እንደሚችልና የሚኒስቴር መ/ቤቱን ገጽታና መልካም ስም በምን ደረጃ ሊጎዳ እንደሚችል አዝማሚያዎችን አስቀድሞ ማጥናትና ለመ/ቤቱ የበላይ አመራር የሙያ ምክር መስጠት፤

- ቀውስ በተከሰተ ጊዜ ስለጉዳዩ በሚገባ ማወቅና ከበላይ አመራር ጋር በመነጋገር ቀዳሚ (Proactive) በመሆን ችግሩ የተከሰተበትን ምክንያት፣ የደረሰውን ጉዳት፣ የተወሰደውን የመከላከል እርምጃና ወደፊት ችግሩ እንዳይከሰት የሚከናወኑ ተግባራትን ሚዲያዎችን በመጠቀም ለህዝብ ማሳወቅ፤

- ቀውሱ ከተወገደ በኋላ የተከናወነውን የኮምዩኒኬሽን ተግባር የያዘ ሙሉ መረጃና ዘገባ ማዘጋጀትና ለበላይ አካል ማቅረብ፤

## 6. አካታች የኮምዩኒኬሽን ሥራዎችን መተግበር

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሴቶች፣ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች በተለየ ሁኔታ አገልግሎቱን ለማዳረስና የበለጠ ተደራሽ ለመሆን በሚያከናውነው ተግባር በኮምዩኒኬሽን መስክ ስትራቴጂያዊ በሆነ መንገድ ዘላቂ ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት የሚከናወኑት ተግባር ከዚህ በታች ቀርበዋል።

- ሴቶችና ወጣቶች በኢንዱስትሪ ዘርፍ በሚከናወኑት ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ግንዛቤያቸውን የማሳደግ፣ አቅማቸውን በመገንባትና በንቃት የማሳተፍ፣ ለመረጃ ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ ተግባራት ይከናወናሉ። በተሰማሩበት መስክ የሚያገኙትን ስኬት ለህዝብ በማሳውቅ ሌሎች ሴቶችና ወጣቶች እንዲሰማሩበትና የሥራ ተሳትፏቸው እንዲጨምር የማበረታታት ሥራዎች ይሠራሉ።

- አካል ጉዳተኞች ልዩ ድጋፍና ትኩረት የሚፈልጉ ህብረተሰብ ክፍሎች በመሆናቸው በኢንደስትሪ ዘርፍ ውስጥ ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ግንዛቤያቸውን በማሳደግ፣ ስኬታማ አካል ጉዳተኞችን በሚዲያ በማስተዋወቅና በማበረታታት እንዲሁም ትኩረት በመስጠት ጥረት የሚያደርጉ ኢንደስትሪዎችን አርአያነት ለህዝብ በማቅረብ ተከታታይ የኮሙኒኬሽን ሥራ ይሠራል።

## 7.ተቋማዊ ማኅበራዊ ሐላፊነትን መወጣት

የመ/ቤቱን አመራር አባላት፣ ሠራተኞች፣ ተጠሪ ተቋማት፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ኢንደስትሪ ቢሮዎችና አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማሳተፍ ዘላቂነት ያለው ተቋማዊ ማህበራዊ ሐላፊነትን የመወጣት ተግባርን የመምራት፣ የማስተባበርና የማስፈጸም የኮምዩኒኬሽን ተግባራት ይከናወናሉ።
እነዚህ ተግባራት በተቻለ መጠን የተቋሙን ልዩ ባሕርይ የተላበሡ እንዲሆኑ ጥረት ይደረጋል። በዚህም መሰረት በተቋማት የሥራ ቦታ የአካባቢ ጥበቃ በማከናወን፣ አመቺ ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅ፣ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች የሥራ እድል የሚፈጥሩበት ስልጠና በመስጠት፣ የየተቋማት ሠራተኞችን ኑሮ ሊደግፉ የሚችሉ የኢንዱስትሪ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ፣ ሰብዓዊ ድጋፍ በመለገስ፣ በሀገር ደረጃ በሚከናወኑ የችግኝ ተከላ፣ ገበታ ለሀገርና የአቅመ ደካሞችን ቤት በጋራ በመሥራትና በመሳሰሉት ላይ በንቃት መሳተፍን ያጠቃልላሉ።

## በምዕራፎች የተከፈለ የስትራቴጂያዊ ግቦች የድርጊት አፈጻጸም እቅድ

| የሚከናወኑ ተግባራት | ምዕራፍ አንድ | | | | | | | | | | | | | | | | ምዕራፍ 2 | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2016 | | | | 2017 | | | | 2018 | | | | 2019 | | | | 2020 | | | | 2021 | | | | 2022 | | | |
| | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | |
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1.ጠንካራና ውጤታማ የውስጥ ኮምዩኒኬሽን መገንባት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የመሥሪያ ቤቱን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ እቅዶች፣ ስኬቶችና ቁልፍ ተቋማዊ ለውጦችን በየጊዜው ማስገንዘብ፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ሠራተኞችን የሚያበረታቱ መርሃ-ግብሮችን ማካሄድ፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ሁሉም የሥራ ክፍሎች በሥራ ክንውኖች ላይ መረጃ ለመለዋወጥ፤ በእቅድና በአፈጻጸም ላይ ለመወያየት መደበኛ ስብሰባዎችን ማካሄድ፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ለሠራተኞች ሥራን የተመለከቱ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን በየጊዜው እንዲያውቁ ማድረግ፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| መሥሪያ ቤቱን የተመለከቱ ማንኛውም መረጃዎች ሠራተኞች በቀላሉ ኤሌክትሮኒክ በሆነ መንገድ የሚያገኙበትን መንገድ መፍጠር፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ሠራተኞች ለበላይና ለመካከለኛ አመራር አባላት በባለቤትነት መንፈስ ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጡ ማበረታታት፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| በየወቅቱ ቅኝት በማደረግ ተጨማሪ የውስጣዊ ኮምዩኒኬሽን ተግባራትን ማከናወን፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የውስጥ ኮምዩኒኬሽን ኦዲት ማካሄድና ውጤቱን ማሳወቅ፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

| የሚከናወኑ ተግባራት | ምዕራፍ አንድ | | | | | | | | | | | | | | | | ምዕራፍ 2 | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2016 | | | | 2017 | | | | 2018 | | | | 2019 | | | | 2020 | | | | 2021 | | | | 2022 | | | |
| | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | | ሩብ ዓመት | | | |
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 4. የቀውስ ጊዜ ኮምዩኒኬሽንን መፈጸም | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ምን አይነት ቀውስ ሊመጣ እንደሚችል አዝማሚያዎችን አስቀድሞ ማጥናትና ለመ/ቤቱ የበላይ አመራር የሙያ ምክር መስጠት፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ቀውስ በተከሰተ ጊዜ ስለጉዳዩ በሚገባ ማወቅና ከበላይ አመራር ጋር በመነጋገር ፕሮአክቲብ በመሆን ለህዝብ ማሳወቅ፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ቀውሱ ከተወገደ በኋላ የተከናወነውን የኮምዩኒኬሽን ተግባር የያዘ ሙሉ መረጃ/ዘገባ ማዘጋጀትና ለበላይ አካል ማቅረብ፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5. አካታች የኮምዩኒኬሽን ሥራዎችን መተግበር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሴቶች፣ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች በተለየ ሁኔታ አገልግሎቱን ለማዳረስና የበለጠ ተደራሽ ለመሆን በሚያከናውነው ተግባር በኮምዩኒኬሽን መስክ ስትራቴጂያዊ በሆነ መንገድ ዘላቂ ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6. ተቋማዊ ማኅበራዊ ሐላፊነትን መወጣት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የመ/ቤቱን አመራር አባላት፣ ሠራተኞች፣ ተጠሪ ተቋማት፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ኢንደስትሪ ቢሮዎችና አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማሳተፍ ዘላቂነት ያለው ተቋማዊ ማህበራዊ ሐላፊነትን የመወጣት ተግባርን የመምራት፣ የማስተባበርና የማስፈጸም የኮምዩኒኬሽን ተግባራት ማከናወን፤ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

# 5. ቁልፍ ስትራቴጂካዊ የኮምዩኒኬሽን መልዕክቶች

## 5.3. የቁልፍ መልዕክቶች ናሙናዎች

የዘርፉ ቁልፍ መልዕክቶች የተቋሙን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች ተገልጋዮች በአግባቡ ተረድተው ለተቋሙ ስኬቶች አብረው እንዲቆሙ የሚያነሳሱና ወደተግባር እንዲገቡ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- ተቋማዊ ብቃትና ግላዊ መሻሻል ለላቀ ኢንዱስትሪ ልማት!
- ኢትዮጵያ ታምርት!
- ኢትዮጵያዊ አምራችነት፣ ከልምምድ ወደ ልማድ!
- ልዩ ትኩረት ለኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪዎች!
- እኛው የኛው አቅም፤ እኛው የኛው ኩራት!
- በሀገሩ ምርት የሚኮራ ትውልድ እንገነባለን!
- ጥራትና ምርታማነት ለውጤታማ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነት!
- የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ለዘላቂ የሥራ ዕድል!
- አብረን ሆነን የጋራ ሐገራችንን እንገነባለን!
- የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት፤ የኢኮኖሚያዊ ነፃነታችን መፃፊያ ወርቃማ ብዕር!
- የቴክኖሎጂ ሽግግርና ፈጠራ ለምርትና ምርታማነት ዕድገት!
- ቀላልና የተሻሻለ ቴክኖሎጂ ለመሠረተ ሠፊ የአምራች ኢንተርፕራይዝ ልማት!
- የቴክኖሎጂ እድገት ለምርታማነት!
- የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት፣ ለጠንካራ ኢኮኖሚ ግንባታ!

ሌሎችም

ከላይ የተጠቀሱት እና ሌሎችም መልዕክቶች እንደየ ጊዜው ሁኔታ ይዘጋጃሉ፡፡

## ሰንጠረዥ3 የውስጥ ስትራቴጂካዊ የኮሚኒኬሽን አቀራረብ

| ተ.ቁ | ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት | የቁልፍ መልዕክት ይዘት | የኮምዩኒኬሽን ዘዴዎች | የኮሚኒኬሽን ማሰራጫ መንገዶች | ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የተቋሙ አመራርና ሠራተኞች | ወቅታዊ ክስተቶች፣ የበዓል መልዕክቶች፣ ሪፖርቶች እቅዶች፣ ስለ ስነ-ምግባር ፣መልካም አስተዳዳር፣ የደህንነት ጉዳዮች፣ የደንበኞች አገልግሎት፣ የሴቶች ጉዳይ፣ የፕሮጀክት ትግበራ፣ ማህበራዊ ሀላፊነቶች፣ | መደበኛና ኢመደበኛ ስብሰባዎች፤ የሠራተኞች ቀን | ስልክ (ቴሌግራም ፣ዋትስ አፕ)፣ የውስጥ እስክሪኖች ማስታወቂያ፣ ህትመቶች (ጋዜጦች፣ ብሮሽሮች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ባነሮች፣ መጽሄቶች) ገጽ-ለገጽ ውይይት፣ ሁነቶች | የጋራ መግባባት፣ የቁርጠኝነት ስሜትንና የሥራ ተነሳሽነትን መጨመር |
| 2 | የተጠሪ ተቋማት አመራርና ሠራተኞች | | መደበኛና ኢመደበኛ ስብሰባዎች | ስልክ(ቴሌግራም ፣ዋትስ አፕ) ገጽ-ለገጽ ውይይት፣ ሁነቶች፣ የስራ ጉብኝቶች፣ ኢግዚቢሽንና ባዛር | መነቃቃት ፣ የተናበበ ቅንጅታዊ አሠራር፣ የተማከለ የመረጃ ሥርዓት መፍጠር፣ መተማመን |
| 3 | የክልል፣ የከተማ አስተዳዳር፣ ኢንዱስትሪ ቢሮ ሐላፊዎች፣ የአምራች ኢንዱስትሪ፣ የኣግሮ ፓርኮች ኮሚኒኬሽን አመራሮችና ሠራተኞች | | መደበኛና ኢመደበኛ ስብሰባዎች፤ የምክክር ስብሰባዎች | ስልክ(ቴሌግራ፣ዋትሳፕየደ) ገጽ-ለገጽ፣ቪዲዮ ኮንቨረስ ስቴሌግራ፣ዋትሳፕየደ፣ገጽ-ለገጽ፣ኢሜል፣ ውይይት፣ሁነቶች፣የስራ ጉብኝቶች፣ ኢግዚብሽንና ባዛር፣(የማስታወቂያ መሳሪያዎች..አጀንዳ፣ኮፍያ፣ቲሸርት፣ቁልፍ ፖስትካርድ…) ፣የሚዲያ ፎረም | መነቃቃት ፣ የተናበበ ቅንጅታዊ አሠራር፣ የተማከለ የመረጃ ሥርዓት መፍጠር፣መተማመን፣ ግልጸኝነት እና ትብብርን መሰረት ያደረገ ግንኙነት የጋራ መግባባት ፣አዳዲስ ሐሳቦች |
| 4 | የተቋሙ ኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት | ወቅታዊ ክስተቶች፣ የበዓል መልዕክቶች፣ ሪፖርቶች እቅዶች፣ ስለ ስነ-ምግባር፣ መልካም አስተዳዳር፣ የደህንነት ጉዳዮች፣ የደንበኞች አገልግሎት፣ የሴቶች ጉዳይ፣ የፕሮጀክት ትግበራ፣ ማህበራዊ ሐላፊነቶች፣ የዘርፉ አምባሳደር ስለመሆን፣ስለ የቅንጅታዊ አሰራርን መዘርጋት ላይ የተኮረ ይዘት ያላቸው መልዕክቶችን መቅረጽ፣ ኤዲቶሪያሎችን ማየት | የቦርድ ስብሰባ | ቴሌግራም፣ገጽ-ለገጽ | የተቋሙን የሚሰሩ የተለያዩ ህትመቶችን መልዕክት/ይዘቶች/ ተቋሙን የሚወከሉ ማድረግ |

# ሰንጠረዥ4 የውጪእስትራቴጂካዊ የኮሚኒኬሽን አቀራረብ

| ተ.ቁ | ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት | የቁልፍ መልዕክት ይዘት | የኮምዩኒኬሽን ዘዴዎች | የኮሚኒኬሽን ማሰራጫ መንገዶች | ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአምራች ኢንዱስትሪዎች ባለቤቶች | ገቢ ምርቶችን መተካት፣ የውጪ ምንዛሬ ግኝት፣ የስራ ዕድል ፈጠራ፣<br>የማምረት አቅም አጠቃቀም፣ የምርት ጥራት፣ የአካባቢ ደህንነት፣<br>ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች<br>የዘርፉ ማበረታቻዎች፣ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች | • ልዩ ልዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የጥናትና የጥቆማ ዕሁፎችን ማሠራጨት<br>• ክፍተትን መሠረት ያደረጉ የገፅ ለገጽ ስልጠናዎች<br>• የዘርፉን ስኬትና ስጋት የሚጠቁሙ ዶክመንተሪዎችን መስራት<br>• ታዋቂ ግለሠቦችን ያካተተ የአደባባይ ሁነት<br>• መረጃ በቀላሉ ለመለዋወጥ የሚያስችል ፕላትፎርም መፍጠር<br>• ልዩ ልዩ ንቅናቄዎች | ቴሌግራም፣ ዋትሳፕ፣ ስልጠና የቲቭና የሬዲዮ ማስታወቂያዎች፣ ዘጋቢ ፊልሞች፣ ፓናል ውይይቶች፣ ልዩ ልዩ ህትመቶች (ብሮሸሮች፣ የጥናት ጆርናሎች፣ ባነሮች፣ ዲጂታል መጽሄቶች) ኢግዚብሽንና ባዛርና ሁነቶች<br>የቴሌቪዥና የሬዲዮ ፕሮግራሞች | የጋራ መግባባት፣ የቁርጠኝነት ስሜትንና የሥራ ተነሳሽነትን መጨመር |
| 2 | መንግስታዊ ተቋማት<br>•ፖሊሲ አውጪዎች<br>•የግብርና እና የማህበራዊ ዘርፍ<br>•የፍትህ ዲሞክራሲ ተቋማት<br>•የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ተቋማት<br>•የመሰረተ ልማት፣ የሳይንስ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ዘርፍ ተቋማት<br>•የሙያና የዘርፍ ማሕበራት | የዘርፉ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች፣ የኢንዱስትሪ ዓብቶች፣ የአካባቢ ሰላምና ደህንነት፣ የብድር አቅርቦት፣ ሀይል አቅርቦት፣ መሰረተ ልማት፣ ቴክኖሎጂና ኢንዱስትሪ ልማት | • የባለሙያዎች አማካሪ ቡድን (think tank) ቡድን እንዲቋቋምና እንዲጠናከር እገዛ ማድረግ<br>• የዘርፉ ስትሪንግ ኮሚቴን ማጠናከር<br>• የዘርፉን የሚዲያ ማሕበር እንዲቋቋም ማገዝና ማጠናከር<br>• ለዘርፉ የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማት እንዲፈጠሩ ግፊት ማድረግ፣ የተቋቋሙትን በስፋት ማስተዋወቅ | ዜናዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ ዘጋቢ ፊልሞች፣ ፓናል ውይይቶች ህትመቶች (የጋዜጦች አምዶች፣ ብሮሸሮች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ባነሮች፣ መጽሄቶች)<br>ሁነቶች<br>ሶሻል ሚዲያ | የተናበበ ቅንጅታዊ አሠራር መዘርጋት እውቀትን መሠረት ያደረገ ድጋፍ ማድረግ አቅም ማደግ<br>በዘርፉ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እድገት |
| 3 | የልማት አጋር ድርጅቶች | የማምረት አቅም አጠቃቀም፣ ምቹ ሁኔታዎች፣ የኢንዱስትሪዎችን አቅም መገንባት፣ ኢንቨስትምንትን መሳብ/ማስተዋወቅ | • የዘርፉን የባለሙያዎች አማካሪ ቡድን (think tank) ንቁ ተሳትፎ ማሳደግ<br>• ኢንቨስት የማድረግ አቅሙ/ፈቃዱ ያላቸውን የሕብረተሠብ ክፍሎች በገጽ ለገጽ ማወያየት<br>• የተመረጡ የኢንቨስትምንት አማራጮችን በመለየት ማስታወቂያዎችን መስራት<br>• በዘርፉ ስኬታማ የሆኑ አምራቾችን ተሞክሮ ማስፋት | ወርክሾፖች፣ ፓናል ውይይቶች፣ ኢግዚብሽንና ባዛር፣ ሶሻል ሚዲያ | ለአምራች ኢንዱስትሪዎች አቅም መጎልበት<br>የሚያግዙ የጥናት፣ የምርምር፣ የማሽነሪና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ድጋፎች ዕድገት<br>በዘርፉ ልማት ዙርያ ያደገ ግንዛቤ |
| 4 | የሚዲያ ተቋም | የተቋሙ አቅዶች፣ ሪፖርቶች፣ አፈጻጸሞች፣ የምርምር ስራዎች፣ የተገኙ ውጤቶች፤ አዳዲስ ምርቶች፤ ተቋማት የሚያዘጋጇቸው ሁነቶች፤ ዓለም አቀፍ ቀናት ሌሎችም | የመስክ ጉብኝቶች፣ጋዜጣዊ መግለጫ፣ፕረስ ኮንፈረንስ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ የውይይት መድረክ ፣ ቃለመጠየቅ፤ ብሮሸር፣ አመታዊ መጽሔት፣ የተለያዩ ሁነቶች ሌሎችም | በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ማሰራጫ ዘዴዎች፣ በጋዜጣና በመጽሔት፤ ዜና፣ ፕሮግራሞች፣ አርቲክል፣ ሐተታዊ ጹፎች፣ የኢንቨስቲጌሽን ዘገባዎች፣ የዶክመንተሪ ሥራዎች፣ የክብ ጠረጴዛ ውይይቶችና በሌሎችም | በአምራች ኢንዱስትሪው ላይ በ30 ፐርሰንት ያደገ አጠቃላይ የዘገባ ሽፋን፣ የተገነባ የተቋም ገጽታ ፣ ለዜጎች ተደራሽ የሆነ ጥራት ያለው የዘርፉ መረጃ፣ በቂ ግንዛቤ ያለው የአምራች ኢንዱስትሪው ጥልቅ ሐተታዊ ጽሁፍ። |
| 5. | የአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ተጠሪ ተቋማትና የተቋሙ የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች | የሕዝብ ግንኙነት ንቅናቄዎችን ማካሄድ፣ እውቀት፣ መረጃና ተሞክሮ ልውውጥ፣ ዘርፉን በጋራ ማስተዋወቅ፣ ቀውስን መከላከል፣ መመከትና ፈጣን ምላሽ መስጠት | የአቅም ግንባታ መድረኮች፣ የዘርፉ የህዝብ ግንኙነት ፎረም ወርክ ሾፖች፣ ዜናዎች፣ የስልክና የኢሜል መረጃ ልውውጦች.. | ገፅ ለገፅ ውይይቶች፣ ማህበራዊ ሚዲያ፣ ሜንስትሪም ሚዲያ፣ ስልክ፣ የቴሌግራም ቡድኖች | በቀውስ ወቅት ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖር ማስቻል፣ ግልጽ መረጃ ለህ/ሰቡ ተደራሽ ማድረግ.. |
| 6. | ሴቶች፣ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች | በዘርፉ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ማስፈን፣ ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ዜጎችን እንቅስቃሴ ተጠቃሚ የማድረግ፤ የሴቶችና ወጣቶች አቅም ግንባታ፤ ለአካል ጉዳተኞች የግንዛቤ ፈጠራ | የህዝብ ክንፍ መድረኮች፣ የቴቪና ሬዲዮ ፕሮግራም፣ የማህበራዊና ሜን ስትሪም ሚዲያ ዜናዎች፣ የህትመት ውጤቶች.. | ሁሉም ማህበራዊ ሚዲያዎች፣ ቴሌቭዥን፣ ሬዲዮ፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች.... | ከዘርፉ ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች፣ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች ቁጥር መጨመር |

## 7. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የብራንዲንግ መርህ

የተቋሙን ስም፣ ዓርማ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶችና ያሉትን እድሎች በማሕበረሰቡ አእምሮ ውስጥ በጠንካራ ጎኑ የመፍጠር ሂደት ነው፡፡ ማሕበረሰቡ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች እንዲረዳ ለማድረግ ግልጽና ወጥ የሆነ የተቋሙ ዓርማና ቀለም ወጥ በሆነ የአቀራረብ ይዘት መከተል ያስፈልገዋል፡፡ ስለሆነም በተቋሙ የሚሠሩ የህትመትና የማስታወቂያ ፕሮዳክሽኖች እንዲሁም የሚዘጋጁ ሁነቶች የተቋሙን ብራንዲንግ ያካተቱ መሆን አለባቸው፡፡


## 8. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኮሚኒኬሽን መዋቅር

የኮምዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪነት ለሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ ሲሆን በስሩ ያሉ ሶስት ክፍሎች ለኮምዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ ይሆናሉ፡፡
በአጠቃላይ መዋቅሩ ያለውን ጠቀሜታ ስንመለከት የበለጠ ስልታዊ አቀራረብን መሰረት ባደረገ መልኩ ኮምዩኒኬት እንዲያደርግ ያስችለዋል፡፡ ይሁን እንጂ መዋቅሩ ራሱ ዓላማዎቹን ለማሳካት በቂ ሀብት፣ የሥራ መሳሪያዎች እና ሠራተኞች ሊኖረው ይገባል፡፡

የተቋሙን ዓይነት፣ ስፋትና ለኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግሩ ያለውን ፋይዳ ስንመለከት ከተጠሪ ተቋማት የኮምዩኒኬሽን ሐላፊዎች፣ ከክልልና ከተማ አስተዳዳር የኢንዱስትሪ ቢሮ ኮሚኒኬሽን ሐላፊዎች፣ ከፓርኮች ኮምዩኒኬሽን ሐላፊዎችና ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ኮምዩኒኬሽን ሐላፊዎች ጋር በቅንጅት የሚንቀሳቀስበት የግንኙነት መዋቅር አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የበለጠ ተቋሙን ገጽታ ለመገንባትና ስኬታማ ለማድረግ ባለሙያዎቹን በትምህርትናና በተግባር ሙያዊ ብቃት ሊኖራቸው የሚያስችል መዋቅር ሊኖረው ይገባል፡፡

እነዚህንና ተመሳሳይ ችግሮችን ለመፍታት በዚህ የግንኙነት ስትራቴጂ ውስጥ የተዘረዘሩትን ተግባራት ለማሳካት ያስችል ዘንድ ተከታዩን መተግበር ያስፈልጋል፡፡

• የኮምዩኒኬሽኑን ሥራ አስፈጻሚ፣ ከተጠሪ ተቋማት የኮምዩኒኬሽን ሐላፊዎች፣ ከክልልና ከተማ አስተዳዳር የኢንዱስትሪ ቢሮ ኮምዩኒኬሽን ሐላፊዎች፣ ከፓርኮች ኮምዩኒኬሽን ሀላፊዎችና ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ኮምዩኒኬሽን ሐላፊዎች መዋቅር በቂ ግብዓት፣ ብቁ የሰው ሀይል ሟሟላት አለበት፡፡
• እንደተቋም የዘርፉን መልዕክት ማርቀቅን በተመለከተ ማዕከላዊ በሆነ አግባብ መመራት ስለሚገባው ይህን ሐላፊነት ለኮምዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ መስጠት፣ አልያም ከስራ አስፈፃሚው ጋር በጋራ መፈፀም ይገባል፡፡
• የተማከለና ተጠያቂነት ያለው የመረጃ ሥርዓት መዘርጋት ይገባል፡፡




## 5.3. የቁልፍ መልዕክቶች ናሙናዎች

## በተቋሙ ውስጥ ያሉ የኮሙዩኒኬሽን ተግባራት /ሥራዎች

የአንድ ተቋም የኮምዩኒኬሽን አደረጃጀት ዋነኛ ተልዕኮ በተቋሙ እንቅስቃሴዎችና በሕዝቡ መሃከል ድልድይ ሆኖ ማገናኘት፤ ሕብረተሰቡ ለተቋሙ ሊኖረው የሚገባውን አጠቃላይ ምስል መወሰንና መምራት፣ ሕብረተሰቡ ከተቋሙ ተልዕኮ ጋር እንዲሠለፍ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ማከናወን ነው፡፡

ዓለም ላይ ለሀገር ኢኮኖሚ ትልቅ ድርሻ ያላቸው በርካታ ተቋማት አሉ፡፡ ነገር ግን የሚሠሯቸውን ሥራዎችና ምርቶች አስመልክቶ በቂ ግንዛቤ ካልፈጠሩና ማስተዋወቅ ካልቻሉ ማሕበረሰቡ ሊያውቀውና ሊጠቀመው አይችልም፡፡ ለዚህም ነው ጠንካራ የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ የሚያስፈልገው፡፡
በዚህ ምክንያት የተቋምን ስም ለመገንባት፣ ግንዛቤንና ድጋፍን ለማግኘት እንዲሁም በሕዝብ አስተያየትና ባህሪ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ጠንካራ የግንኙነት መስመር መመስረት አስፈላጊ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርም እንደ ማንኛውም ግዙፍ ሀገራዊ ተቋም በዚህ መሠረታዊ የመረጃ ስርጭትና የተልዕኮ ስርፀት መርህ ይመራል፡፡

በዚህም መሠረት የሕዝብ ግንኙነትና ኮምዩኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ በዚህ ስትራቴጂ ትግበራ የሚከተሉትን ኃላፊነቶች መወጣት ይኖርበታል፦

- የተቋሙን መልካም ገጽታ ለመገንባት የሚስችሉ ልዩ ልዩ የብራንዲንግ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል የኮምዩኒኬሽን /የግንኙነት እቅድ/ ማዘጋጀት፤

- የተቋሙ ቃል አቀባይ/የመረጃ የትኩረት ነጥብ ሆኖ መሥራት፣
- በከፍተኛ አመራሩና በማኔጅመንት የሚሰጡ አቅጣጫዎችን በኮምዩኒኬሽን ዕይታ ቃኝቶ መፈጸምና ማስፈጸም፤

- በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ውስጥ በተለያዩ ዋናና ደጋፊ ሂደቶች መካከል የመረጃ መረብን ማቋቋም፣ ማስተዳደርና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ፣

- ለተቋሙ ራዕይና ስኬት የሚረዱ የተለያዩ የሕዝብ ግንኙነት ዝግጅቶችን ማቀድ፣ ማስተባበር፣ ማስፈፀምና የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ፤

- ለሚዲያ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠትና ሁሉም ምላሾች በህዝብ ግንኙነት ወይም በሚኒስቴሩ ውስጥ በሚመለከታቸው ሌሎች አካላት መሰጠታቸውን ማረጋገጥ፣

- የዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ የሚዲያ ሪፖርቶችን በመከታተል፣ ሁኔታዊ ትንተናዎችን በማካሄድና የህዝብና የባለሙያ አስተያየቶችን በመመርመር ለተገቢ ርምጃ የሚረዱ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፣

- ከሚመለከታቸው አካላት ትክክለኛ ፈቃድ ለሚያቀርቡ የውጭ ጋዜጠኞችና የፊልም ባለሙያዎች መረጃ እና ድጋፍ መስጠት፣

- የመረጃ ግልፅነትን ለማስጠበቅና በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች ላይ ብሔራዊ መግባባትን ለማሳደግ የፓናል ውይይቶችንና ልዩ ልዩ መድረኮችን ማደራጀት፣

- የአምራች ኢንዱስትሪ ስትራቴጂክ ዕቅዶችን አስመልክተው የሚዘጋጁ መድረኮች፣ ርዕሰ ጉዳዮች፣ አጀንዳዎችና መልዕክቶች የዘርፉን ውጤታማነትና ተቀባይነት የሚያፋጥኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- የሚመለከታቸው አካላትን የሚያሳትፉ ልዩ ልዩ የመስክ ጉብኝቶችን በማዘጋጀት ዘርፉን ማስተዋወቅ፣



# ምዕራፍ አራት


## 5. ኮምዩኒኬሽን ፕሮቶኮል

### 5.1. ከኮምዩኒኬሽን አንፃር ያሉ የህግ ጉዳዮች

የኮምዩኒኬሽን ፕሮቶኮሉ የመገናኛ ብዙሀንና መረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000 መሰረት ያደረገ ሲሆን፤ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃን እንዴት እንደሚገልፅና እንደሚያሰራጭ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ከማረጋገጥ አኳያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

#### 5.1.1. መረጃ የማግኘት መብት

ተቋሙ በዚህ ስትራቴጂ መሰረት መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ህጋዊ ተቋም ወይም ግለሰብ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚሰጠውን አገልግሎትና ማንኛውንም ዓይነት መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡




ምስል 2. የመረጃ ፍሰት ዘዴዎች



# ምዕራፍ አምስት

## 5. ክትትልና ግምገማ

ክትትልና ግምገማ የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ግቦችን ለማሳካት በተጨባጭ ለማረጋገጥና የፕሮግራሙን አፈጻጸም ለመከታተል አስፈላጊ ሲሆኑን በክትትል ሂደት ላይ ያለውን ሥራ ይገመግማል፣ የእንቅስቃሴዎችን አተገባበርና ከተቋሙ ግቦችና ዓላማዎች ጋር አብሮ መሄዳቸውን ያገናዝባል ያረጋግጣል። የተመለከቱትን መርሆዎች በመከተል የስትራቴጂውን ዓላማና ግቦች፣ የማስፈጸሚያ ስልቶችና አካሄዶች መሰረት በማድረግ የኮምዩኒኬሽንን ሥራ ዕቅድ ዝግጅት፣ ድጋፍና ክትትል ግምገማ ሥርዓት የሚከተሉትን መሰረታዊ አካሄድ ተከትሎ ይተገበራል።

የሂደት ክትትል፡- በታቀደው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተግባራት እንዴት እንደሚከናወኑ ሂደቱን ይከታተላል፤ የገንዘብ ክትትል፡- የተመደበው በጀት በአግባቡ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑንና አለመሆኑን መከታታል፤ የውጤቶች ክትትል፡- ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ግብ አንጻር እንቅስቃሴው ውጤት ምን እንደሚመስል መከታታል።

### የመገምገሚያ መስፈርቶች

አግባብነት፡- ተግባሮቹ ምን ያህል ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፖሊሲ የሚስማማ ነው።
ውጤታማነት፡- እንቅስቀሴው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን ዓላማዎችን ምን ያህል አሳካ የሚለው፤

### 5.1. የዕቅድ ዝግጅት ሥርዓት

የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂውን ማሳካት የሚቻለው ግልፅ የሆነና የተናበበ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድ አዘጋጅቶ በመሥራት ነው። በመሆኑም የኮምዩኒኬሽን ዕቅዱም ዓመታዊና የአራት ዓመት እና የሰባት ዓመት ዕቅድ በሚል በበጀት ዓመታት ጊዜ የተከፋፈለ አሠራርን ይከተላል።

### 5.2. የድጋፍና ክትትል ሥርዓት

ስትራቴጂውን ተከትሎ የሚወጣውን እቅድ በተቀመጠው ጊዜና ጥራት ለማሳካት እንዲቻል በዕቅድ አወጣጥ ጊዜና በትግበራ ሂደት ጥራቱን የጠበቀና ተከታታይነት ያላቸው የድጋፍ፣ የክትትልና የግምገማ ሥራዎች ይሠራሉ። የክትትል ሥራዎችም ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ይከናወናሉ።

## 5.3. የግምገማ ሥርዓት

የኮምዩኒኬሽን ሥራ የትግበራ አፈጻጸም የግምገማ ሥርዓት ውጤትን መለካት የሚያስችል እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## በዚህም መሠረት :-

- ስትራቴጂው ጸድቆ ወደ ሥራ ከተገባበት ጊዜ ጀምሮ በእቅድ አፈጻጸም ላይ ወቅታዊ የሪፖርት ልውውጥ በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት፣ በዘጠኝ ወራት እና በዓመት ማድረግ፣
- በተጠሪ ተቋማት፣ በክልልና ከተማ አስተዳደር፣ በፓርኮች፣ በአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚገኙ የሕዝብ ግንኑነትና ኮሚዩኒኬሽን አደረጃጀቶች የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት፣ በዘጠኝ ወራት እና በዓመት እንዲለኩ በማድረግ የጋራ የምክክር መድረኮችን ማካሄድ፤
- በአፈጻጸም ሂደት በሚያጋጥሙ ችግሮችና ክፍተቶች ላይ ለፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- በተጠሪ ተቋማት፣ በክልልና ከተማ አስተዳደር፣ በፓርኮች፣ በአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚገኙ የሕዝብ ግንኑነትና ኮምዩኒኬሽን በመገኘት በዓመት ሁለት ጊዜ የመስክ ምልከታ በማድረግ ግብረመልስ መስጠት፣
- የሚዲያ ፎረሙን በዓመት ሁለት ጊዜ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት የነበረው የመረጃ ፍሰትና የተቋሙን ገጽታ በተመለከተ ጠቃሚ ሐሳብና ተሞክሮዎችን ማሠባሠብ

## 5.4 ማስፈጸሚያ ስልት

- ኤዲቶሪያል ፖሊሲ፣
- ሀውስ ስታይል
- የኮምዩኒኬሽን የሥራ መመሪያ፤
- የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም መመሪያ እና ሌሎችም ይዘጋጃሉ፡፡

# 13. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

## 13.1. የኮምዩኒኬሽን አደረጃጀት

የሚኒስቴር መ/ቤቱን የኮምዩኒኬሽን አደረጃጀት በበቂ የሠው ሃይልና ቁሳቁስ የተሟላ እንዲሆን ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት አሁን ያለውንና ስትራቴጂውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆነውን የሠው ሃይል የሚጠቁም ሠንጠረዥ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

| የሥራ መደብ | አሁን ያለው የሰው ኃይል ብዛት | ለሥራው የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት |
|---|---|---|
| የኮምዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ | 1 | 1 |
| ጸሐፊ | 1 | 1 |
| ቡድን/ዴስክ ሐላፊ | - | 2 |
| ከፍተኛ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች | - | 3 |
| የሶሻል ሚዲያ ባለሙያ | - | 1 |
| የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች/ኤዲተሮች | - | 2 |
| ቪዲዮና ፎቶግራፍ ባለሙያዎችና ዶክመንቴሽን | 1 | 2 |
| ግራፊክስ ዲዛይነርና ፊልም ኤዲተር | - | 1 |
| የዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያ | - | 1 |
| ቤተ-መጻሕፍት ባለሙያ | 2 | 3 |
| ድምር | 5 | 17 |

## 13.2. ለኮሞዩኒኬሽን የሥራ መሳሪያ ፍላጎት

ለስትራቴጂው ስኬት ከዚህ በታች ያሉ የኦዲዮቪዥዋል መሳርያዎችን ማሟላት ያስፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የእቃው ዓይነት | የሚያስፈልገው የእቃ ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የድምጽና ምስል ቀረጻ የሚካሄድበት ስቱዲዮ ግንባታ | 1 | |
| 2 | ጥራት ያለው ምስል የሚያነሱ የኤች ዲ የካሜራ ግር | 2 | |
| 3 | የጠረጴዛ ማይክና ሎጎ | 3 | |
| 4 | የድምፅና ምስል ኤዲቲንግ ኮምፒዩተር | 2 | |
| 5 | ኤል ዲ መብራትና ተያያዥ መሳሪያዎች | ፓኬጅ | |
| 6 | የተለያዩ ማይኮች | ፓኬጅ | |
| 7 | የስቱዲዮ ዴስክና ወንበሮች | ፓኬጅ | |
| 8 | ሌሎች አስፈላጊ መሳሪያዎች | | |

## 7. ማጠቃለያ

የስትራቴጂው ዋነኛ ዓላማ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ስትራቴጂያዊ እቅድ፣ ራዕይና ተልዕኮ በውጤታማ የኮምዩኒኬሽን ሥራዎች ማሳካት እንዲሁም የተቋሙ ሠራተኞችና አመራሮች የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎችን ለተቋሙ ሠራተኞች፣ ለተገልጋይ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ በማድረግ የተቋሙን ገጽታ መገንባትና በኅብረተሰቡና በተቋሙ መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ የኮምዩኒኬሽን ሥራ መሥራት ነው፡፡

በመሆኑም ይህ ስትራቴጂ የማኅበረሰቡን ተሳትፎ የሚያበረታቱ፣ ኢንዱስትሪዎችንና ምርታቸውን የሚያስተዋውቁ፣ የሀገር ውስጥ ምርቶችን የመጠቀም ባሕል የሚያሻሽሉና ዘርፉን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ልምድና ተሞክሮዎችን የሚያሳልጡ የውስጥና የውጪ ግንኙነትን የሚያጠናክሩ የሕዝብ ግንኙነትና ኮምዩኒኬሽን ሥራዎችን የያዘ ነው፡፡

በዚህ ሂደትም የተቋሙን ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላትን ለመለየት ተችሏል፡፡ ለያንዳንዱ ተደራሲ የሠጥቶ መቀበል ሚና ትንተና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ስትራቴጂ አስፈጻሚው ክፍል ከተለያዩ ዘርፎችና የሥራ ክፍሎች ጋር በሚያደርገው ትስስር /Interface/፣ ቅንጅት፣ ትብብርና አሳታፊነት የመረጃ ቅብብሎሹን ሥራ ማቀላጠፍ እንዲቻል አሠራር አስቀምጧል፡፡

ተቋሙ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፉ ላይ እያከናወነ ያለውን ዋና ዋና ተግባራት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግና መልዕክቶችን ለመቅረጽ የማሳወቅና ማስተማር /Information & Education/፣ የማሳመንና ንቅናቄ የመፍጠር /Persuasion & Moblization/ እና የማነቃቃትና ተፅእኖ የመፍጠር /motivating & Influencing/ ማዕቀፎችን እንዲሁም የአብሮነትና የባለቤትነት ስሜት መፍጠር (inclusive and ownership)ን መሰረት በማድረግ ስትራቴጂው ቀርቧል፡፡

በመሆኑም በዚህ ስትራቴጂ የታለሙ ዓበይት እቅዶች ከግብ እንዲደርሱና በሀገራዊው የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴ የሚፈለገውን ድጋፍ ማበርከት እንዲችሉ በተለይ የሚኒስቴሩ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች ለስራው ተገቢውን ትኩረትና ድጋፍ መስጠት፣ በየወቅቱ ሒደቱን መከታተልና ማስተካከያና ማሻሻያዎችን ማድረግ፣ እንዲሁም አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመጨረሻም ይህን ስትራቴጂ ለማስተግበር ኃላፊነቱ የተሠጣቸው የሥራ ክፍሎችና ባለሙያዎች የሥራውን ክብደት፣ ሳይንሳዊነትና ሀገራዊ ሐላፊነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ሒደት ከፍተኛ ቁርጠኝነትና የባለቤትነት መንፈስ ሊፈጽሙት ይገባል፡፡

# የኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ በጀት

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | የበጀት ምንጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በውል ለሚፈጸሙ አገልግሎቶች/ የሚዲያ፣ የስክሪንና ቴሌኮም ኮንትራት (579,824,00 ብር) | | | | | | | | |
| 1.1 | በኢንዱስትሪ ዘርፉ ዙሪያ በየዓመቱ 2 ዶክመንተሪዎችና 3 ፓናል ውይይቶችን በማዘጋጀት ማሠራጨት | 240,000 | 480,000 | 720,000 | 960,000 | 1,200,000 | 1,440,000 | 1,680,000 | ከመደበኛ በጀትና ፕሮጀክት በጀት |
| 1.2 | በኢንዱስትሪ ዘርፉ በየዓመቱ 5 አጫጭር የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎችን ማሰራትና ማሠራጨት | 200,000 | 400,000 | 600,000 | 800,000 | 1,000,000 | 1,200,000 | 1,400,000 | |
| 1.3 | ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር የሚገባ አመታዊ ውል የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምድ (አማርኛ)፣ | 40,800 | 81,600 | 122,400 | 163,200 | 204,000 | 244,800 | 285,600 | |
| 1.4 | ከብሮድካስት ሚዲያ ጋር 1 የሬዲዮና 1 የቴሌቪዥን ሳምንታዊ ፕሮግራም ማዘጋጀትና ማሠራጨት | 1,440,000 | 2,880,000 | 4,320,000 | 5,760,000 | 7,200,000 | 8,640,000 | 10,080,000 | |
| 1.5 | በየዓመቱ 5 የተለያዩ የተቋም ሁነቶችንና የካላንደር በዓላትን አስመልክቶ በአጭር የፅሁፍ መልዕክት መልዕክቶችን ማሰራጨት | 50,000 | 100,000 | 150,000 | 200,000 | 250,000 | 300,000 | 350,000 | |
| | በየዓመቱ በ5 የተለያዩ አጀንዳዎች ዙርያ የሚያተኩሩ አጫጭር መልዕክቶችን የያዙ ማስታወቂያዎችን ለተከታታይ 10 ቀናት በ10 ዋና ዋና ከተሞች በሚገኙ 20 ስክሪኖች ላይ ለማሠራጨት | 100,000 | 200,000 | 300,000 | 400,000 | 500,000 | 600,000 | 700,000 | |
| 2 | በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን ለማስፈፀም የሚውሉ ወጪዎች (10,920,000 ብር) | | | | | | | | |
| 2.1 | በየዓመቱ ሐገራዊውን የዘርፉን እንቅስቃሴ የሚያሳዩ 10 የዕቅድ ዜናዎችንን ለማዘጋጀት | 30,000 | 60,000 | 90,000 | 120,000 | 150,000 | 180,000 | 210,000 | ከመደበኛ በጀት |
| | በየዓመቱ 2 ጊዜ ከዘርፉ የህዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ተቋማት/ የሚዲያ ፎረም/ሰሰ ጋር ምክክር ለማድረግ | 80,000 | 160,000 | 240,000 | 320,000 | 400,000 | 480,000 | 560,000 | |
| 2.2 | በየዓመቱ አንድ የኢንዱስትሪ ዘርፉን ተጨባጭ እንቅስቃሴዎች ለሚዲያ አካላት ለማሳየት (ለሚዲያ ጉብኝት) | 60,000 | 120,000 | 180,000 | 240,000 | 300,000 | 360,000 | 420,000 | |
| 2.3 | በየዓመቱ በዘርፉ አጀንዳዎች ዙርያ አስፈላጊ የሆነ ትኩረትና ግንዛቤን ለማስፋትና ተቋማዊ የውስጥ ግንኙነትን ለማጠናከር የሚያስችሉ 6 ሁነቶችን ለማዘጋጀት | 220,000 | 440,000 | 660,000 | 880,000 | 1,100,000 | 1,320,000 | 1,540,000 | |
| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | የበጀት ምንጭ |
| 3 | በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራትን ለማጉላት፣ የተገኙ የጥናትና ምርምር ውጤቶች፣ ሀገር ዓቀፍና ዓለማቀፍ ተሞክሮዎች፣ የአሠራር ስርዓት መግለጫዎችንና መሥል የሕትመት ውጤቶችን ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ (2,940,000 ብር) | | | | | | | | |
| 3.1 | በየዓመቱ አንድ ልዩ አመታዊ መጽሔት በ1,000 ኮፒ ለማሳተምና ለማሠራጨት | 12,000 | 24,000 | 36,000 | 48,000 | 60,000 | 72,000 | 84,000 | ከመደበኛ በጀት |
| 3.2 | በየዓመቱ አንድ የጥናት ጆርናል በ400 ኮፒ ለማሳተምና ለማሠራጨት | 12,000 | 24,000 | 36,000 | 48,000 | 60,000 | 72,000 | 84,000 | |
| 3.3 | በየዓመቱ 4 ዓይነት ብሮሽሮች፣ 2 ቡክሌቶችን እንዲሁም 4 በራሪ ወረቀቶችን እያንዳንዳቸውን በ2,000 ኮፒ ለማሳተምና ለማሠራጨት እንዲሁም ልዩ ልዩ የ4 ፖስተርና መሠል ዲዛይኖችን ለማከናወን | 27,000 | 54,000 | 81,000 | 108,000 | 135,000 | 162,000 | 189,000 | |
| 3.4 | በየዓመቱ 4 የዜና መፅሔትን በ500 ኮፒ ማሳተምና ማሠራጨት | 40,000 | 80,000 | 120,000 | 160,000 | 200,000 | 240,000 | 280,000 | |
| 3.4 | በየዓመቱ 4 የበዓል ፖስት ካርድ እና 2 አይነት የጥሪ ካርድ እያንዳንዳቸውን በ500 ኮፒ ለማዘጋጀትና ለማሠራጨት | 10,000 | 20,000 | 30,000 | 40,000 | 50,000 | 60,000 | 70,000 | |
| 3.5 | በየዓመቱ ወቅታዊ መልዕክቶችን የያዙ 40 መደበኛና 20 ሮል አፕ ባነሮችን ለማሳተም | 4,000 | 8,000 | 12,000 | 16,000 | 20,000 | 24,000 | 28,000 | |
| 4 | የተቋሙን ገፅታ የሚያጎሉና ልዩ ልዩ ሁነቶችን ታሳቢ ያደረጉ የብራንዲንግ ስራዎችን ለማከናወን (53,200,000 ብር) | | | | | | | | |
| 4.1 | የተለያዩ ሁነቶችን ታሳቢ በማድረግ 400 የተቋሙ ሎጎ ያለበትን የእጅ ባንዲራዎችን ማሳተም | 40,000 | 80,000 | 120,000 | 160,000 | 200,000 | 240,000 | 280,000 | ከመደበኛ በጀት |
| 4.2 | በየዓመቱ አንድ ደረጃውን የጠበቀ አጀንዳ በ1,000 ኮፒ፣ እንዲሁም 2,000 ኮፒ ማስታወሻ ደብተር በማሳተም ማሠራጨት | 60,000 | 120,000 | 180,000 | 240,000 | 300,000 | 360,000 | 420,000 | |
| 4.3 | በየዓመቱ አንድ ወቅታዊ መልእክቶችን የያዘ የጠረጴዛ ካላንደር በ500 ኮፒ ማሳተምና ማሠራጨት | 10,000 | 20,000 | 30,000 | 40,000 | 50,000 | 60,000 | 70,000 | |
| 4.4 | በየዓመቱ የተቋሙ ሎጎ የታተመባቸው 800 ቦርሳዎች፣ 200 ዣንጥላዎችና 200 ፍላሽ ዲስኮች እንዲሁም 500 እስክሪብቶዎችን በማዘጋጀት ማሠራጨት | 80,000 | 160,000 | 240,000 | 320,000 | 400,000 | 480,000 | 560,000 | |
| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | የበጀት ምንጭ |
| | ድምር | 2,755,800 | 5,511,600 | 8,267,400 | 11,023,200 | 13,779,000 | 16,534,800 | 19,290,600 | |
| | መጠባበቂያ 5% | 137,790 | 275,580 | 413,370 | 551,160 | 688,950 | 826,740 | 964,530 | |
| | ጠቅላላ ድምር | 2,893,590 | 5,787,180 | 8,680,770 | 11,574,360 | 14,467,950 | 17,361,540 | 20,255,130 | |
| | አጠቃላይ የኮሙኒኬሽን ስራዎች አስፈላጊ በጀት | 81,020,5020 | | | | | | | |

ሚያዚያ 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ